# ፍቅርና ሰላም

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚታተም ወርሃዊ ጋዜጣ

A Monthly Amharic/English Newspaper Published by the Catholic Bishop's Conference of Ethiopia (CBCE) General Secretariat/ECS

# LINK

ቁጥር 565 | ግንቦት 2016 ዓ.ም | ዋጋው የኢት. 15.00 ብር


03 ወራት ቀረው

ካቶሊካዊ ሲኖዶስ 2014 2016

ለሲኖዶሳዊት ቤተ ክርስቲያን

ኅብረት / ተሳትፎ / ተልእኮ



## የኢ.ፌ.ደ.ሪ. ትምህርት ሚኒስትር ክቡር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ዩኒቨርስቲን ጎበኙ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ትምህርት ሚኒስትር ክቡር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ አዲስ አበባ፥ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን እና በቅዱስ ቶማስ አኳይነስ ስም የተሰየመውን የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የሆነውን ኢኩስታ (Ethiopian Catholic University St Thomas Aquiuness -ECUSTA) ሚያዝያ 8 ቀን 2016 ዓ.ም. ከብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ፕሬዚዳንት፣ ከብፁዕ አቡነ ሉቃስ የእምድብር ሃገረ ስብከት ተተኪ ጳጳስ፣ ከክቡር አባ ዳንኤል ሃሶ በኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን ጠቅላይ ጽ/ቤት የትምህርት ክፍል ሃላፊ እና ከከፍተኛ የሥራ ሃላፊዎች ጋር በመሆን ጎብኝተዋል።

ገፅ 3



## ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል።

ሉቃ. ፩:፵፰

የማርያም ወር

## በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የሶዶ ሀገረስብከት ማህበራዊ እና ልማት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የ"ምድር ቀን" አከበረ



የ "Earth Day" እ.አ.አ ከ1970 ጀምሮ በዩናይትድ ስቴትስ ኮሌጆች እና ካምፓሶች መከበር የጀመረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በመላው ዓለም በየዓመቱ እ.አ.አ ሚያዚያ 22 ይከበራል።

ገፅ 3

## Message Of His Holiness Pope Francis For The First World Children's Day

WORLD CHILDREN'S DAY
ROME 2024

Page 10

የብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ የ25ተኛ የጵጵስና የብሩራዊ ኢዮቤልዩ ዓመትን በማስመልከት ሥጦታ ለማቅረብ ለሚፈልጉ ሁሉ የቁሳዊ ሥጦታ ቀርቶ የትምህርት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወጣቶች እንደሚውል በማሰብ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ የሚል የገንዘብ ድጋፍ ዕድል መመቻቸቱን ገልጸው በተዘጋጀው የባንክ አካውንት መላው ካቶሊካውያን እና በጎ ፍቃድ ያላቸው ሁሉ ለዚህ በጎ አድራጎት ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

**Cardinal Berhaneyesus Fund**

Account Name: **Cardinal Berhaneyesus Fund**
Account Number: **1000523294338**
Commercial Bank of Ethiopia, Mahatema Gandhi Branch
Swift Code: **CBETETAA**

# ፍቅርና ሰላም

መስከረም 1967 ዓ. ም. ተጀመረ

አሳታሚ ቤተ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የማኅበራዊ መገናኛና ሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ በየወሩ ተዘጋጅቶ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

| | |
|---|---|
| ዋና አዘጋጅ | አባ አበራ ማኬቦ |
| ምክትል ዋና አዘጋጅ | አቤል ሙሴ |
| ማኔጂንግ ኤዲተር | ቤዛዊት አሰፋ |
| ተቀዳሚ ረዳት አዘጋጅና ሪፖርተር/ኤዲተር | ገብሩ ሃ/ዮሐንስ |
| ምክትል ረዳት አዘጋጅ | መሳይ ማሪዮ |

| | |
|---|---|
| ፕሩፍ ሪደር | የምሥራች አሰፋ |
| ሌይ አውት 1 | ቤተልሔም ታደሰ |
| ሌይ አውት 2 | ጨረቃ ዘውዴ |
| ስርጭት | ማኅበራዊ መገናኛና ሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ |


ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ ስልክ - (0111) 55 03 00 ፋክስ (0111) 55 31 13 E-Mail - scpr@eccsdco.org Website - https//www.cbce-gs.org

# ርዕሰ አንቀጽ

## ካቶሊካዊ እምነታችን ጉዞ

**``ካቶሊክ``** የሚለው ቃል የግሪክ ሥነ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ሁሉንም የሚያካትት፣ የሚያቅፍ ፣ ሁሉንም ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ፣ የሁሉ የሆነ የግዕዝ እንተ ላዕለ ኵሉ የሚለውን ቃል ይተከዋል። ለመጀመሪያ ጊዜ **``ካቶሊክ``** የሚለው ቃል የተጠቀመው በ107 ዓ.ም ቅዱስ ኢግናጢዮስ የተባለው የወንጌላዊ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ተማሪ ነበር። ቅዱሱ ይህንን ቃል የተጠቀመው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገኝበት ቦታ ሁሉ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን እንደምትገኝ፤ክርስቶስ የሁሉ መሆኑና በቦታ፣ በዘር፣ በጎሳ፣ በቋንቋ፣ ሆነ በነገድ የተወሰነ ላለመሆኑ ከመምህሩና ራሱ የኖረበትን የክርሰትና ሕይወት ተመከአሮ ይመሰክራል። በ325 ዓ.ም በኒቂያ ጉባኤ የተደነገገውም የሐዋርያት ጸሎተ ሃይማኖት የእውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን መገለጫ የሆነውን **“አንዲት፣ ቅድስት፣ ካቶሊካዊት ፣ሐዋርያዊት”** ናት በመባል የተደነገገውን የአበው ውሳኔ የበለጠ አጠናክሮታል።

ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ ስለሆነና ሁሉም ሕዝቦች ደግሞ የክርሰቶስ አካል ክፍሎች ስለሆኑ ቤተክርስቲያን ካቶሊካዊት ትባላለች። ካቶሊካዊት የተባለችውም በውስጥዋ ማንንም ገለልተኛ ሳታደርግ ሁሉንም የምታካትት በመሆኗ ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰብዓዊነቱ እንደ ሰው በዚህ ምድር እንደኖረ ፣ የሰዎችን ኃዘን ለመጋራት እንዳዘነና እንዳለቀሰ እንዲሁም እንደማንኛውም ሰው ድካም ይሰማው እንደነበረ ታስተምራለች (ሉቃ 22፡-44)። በተመሳሳይ መልኩ ስለ ኃጢአታችን እንደሞተ ነገር ግን በአምላክነቱ ሞትን ድል አድርጎ እንደተነሳ ታምናለች፣ ታስተምራለች። ይህም ማለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን የእምነቷ መሰረት ስለሆነ ካቶሊካዊት ትባላለች።

ክርስቶስ ሐዋርያትን ሲልካቸው ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ የእኔ ደቀ መዝሙር አድርጓቸው ( ማቴ 28፡-19) ባለው ትዕዛዝ ቤተ ክርስቲያን ይህንን መሠረት አድርጋ በዓለም ሁሉ ቃሉን የማስተማር፣ የማጥመቅና የጌታ ደቀ መዛሙርት የማድረግ ሥራ ስለምታከናውን ካቶሊካዊት ትባላለች።

የእግዚአብሔር መንግሥት ለሁሉም የተከፈተና የእግዚአብሔር ቤተሰበ መሆን የሚችለው ሁሉም እንደሆነ በዓለም ዙሪያ በተለያየ ባህልና ቋንቋ ለተለያየ ሕዝብ ስለምታስተምር ካቶሊካዊት ትባላለች።

መጽሐፍ ቅዱስና ቱውፊት በሁለት እጆችዋ ይዛ ታስተምራለች። በእርግጥ መጽሐፍ

> **"የእግዚአብሔር መንግሥት ለሁሉም የተከፈተና የእግዚአብሔር ቤተሰበ መሆን የሚችለው ሁሉም እንደሆነ በዓለም ዙሪያ በተለያየ ባህልና ቋንቋ ለተለያየ ሕዝብ ስለምታስተምር ካቶሊካዊት ትባላለች"**

ቅዱስ ዋና የሕይወት መመሪያ ሲሆን ነገር ግን መጻሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተካተቱ የቤተክርስቲያን አስተምህሮ የምትቀበልና የምታስተምር በመሆንዋ ካቶሊካዊት ትባላለች።።

ከዚህም በተጨማሪ የራስዋ የሆነ ዶክትሪን ያላት ቤተክርስቲያን ስትሆን በጿጋ ምንጭነታቸው የሚታወቁትን ሰባቱ የቤተክርስቲያን ምሥጢራት ተቀብላ ምዕመናን ታንጻለች ትመግባለች።

የተደራጀና የዳበረ አምልኮ (የሊጡርጊያ) ሥርዓት ያላትና ተለያየ ፀሎት አደራረግ መንገድ የምትከተል ቤተክርስቲያን ነች። የተለያየ የአምልኮ ሥርዓተ ማለት የምሥራቅና የምዕራብ ሥርዓተ አምልኮ እንደ ትልቅ ሀብት ይዛ የምትጠቀም ቤተክርስቲያን ናት።

የሰው ልጅ በነፍስና በሥጋ እንደቆመም በመረዳት የተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የምታበረታታና በእነዚህ አማካይነት ለሁለንተናዊ ሰብዓዊ ዕድገት በማሰብ ልዩ ልዩ አገልግሎት ለማህበረሰቡ የምትሰጥ ቤተክርስቲያን ናት።

ለሰብዓዊ ክብር ወይም ለሕይወት ክብር ትልቅ ዋጋ በመስጠት ታስተምራለች። ሕይወት ከማህፀን ጀምሮ መከበር አለበት በማለት ስለ ድምጸ የለሽ ፍጥረታት ወይም ስለ አቅመ ላጡ ለተጎዱ ድምጿዋን ከፍ አድርጋ ትናገራለች።

ለተፈጥሮ ጥበቃ ለአየር ንብረት ለውጥ ልዩ ትኩረት በመስጠት ትሰራለች ታስተምራለች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በትብብር ትስራለች።

በረጂም ዘመናት ካላት ልምድ በመነሳት በመከባበርና በመተጋገዝ ከሌላ የእምነት ተቋማት ጋር ገንቢ የሆኑ ውይይት በማድረግ ተቻችሎና ተባብሮ የመኖር፣ የመስራት መንፈስና ባህል እንዲዳብር ግንባር ቀደም ሆና ድርሻዋን እያበረከተች ትገኛለች።

በአደረጃጀቷም ካቶሊካዊት ቤተክርቲያን ሁሉንም የሚያካትት አስተዳደራዊ መዋቅር ያላት ሲሆን ይህም ከርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጀምሮ በተለያየ ደረጃ የሚመሩዋትና የሚያገለግሏት ጳጳሳት፣ ካህናት፣ መነኮሳት ፣ደናግል፣ ምዕመናን እያሳተፈች ለቤተክርስቲያን ዕድገትና ለሕዝቦች ደኅንነት ተልኮዋን ትወጣለች።

ዛሬም ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል የተመሠረተች በሐዋርያት ዓምድ የታነጸች ፤ በሐዋርያው ጴጥሮስ ተተኪ በሆኑት በርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት የምትመራ ቤተ ክርስቲያን ናት።

ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በመላው ዓለም ከ1.3 በላይ ቢሊዮን አማኝ ያላት ፤ አንድ ድምጽ ትናገራለች፣ በአንድ መመሪያና ደንብ ትተዳደራለች፣ እንደ አንደ መንጋ በአንድ እረኛ ትመራለች።ጥሩ መሪ የእግዚአብሔርን ተልዕኮ በግንባር የተቀበለና የተጣለበትን አደራ ከሕዝቡ ጋር ሆኖ የሚፈጽም ሆኖ ስለሚታመንበት ነው። መሪን የሚመርጠው መንፈስ ቅዱስ ነው። ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ በዘመናችን ይህችን ታላቅ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሊመሩ የተመረጡ የአገልጋዮች አገልጋይ ናቸው።

**ወሰብሐት ለእግዚአብሔር**

## የዕርቀ ሰላም ጸሎት

ፈጣሪ ሆይ
የሰላም መሳሪያ እንድንሆን
አድርገን።
ጥላቻ ባለበት ፍቅር፤
በደል ባለበት ይቅርታ፤
ክርክር ባለበት ስምምነት፤
ጥርጣሬ ባለበት መተማመን፤
ሐዘን ባለበት ደስታ፤
ጨለማ ባለበት ብርሃን፤
እንዲገኝ እናደርግ ዘንድ አብቃን።
ፈጣሪ ሆይ፤
በሕዝባችን መካከል ዕርቅ
ይውረድ፤
ሰላምህ ይስፈን፤
አገራችን ኢትዮጵያን ባርክልን
ጠብቅልን።
አሜን!

## የሲኖዶሳዊ ጉዞ ጸሎት

**መንፈስ ቅዱስ ሆይ! ና!**
**እነሆ በስምህ ተሰብስበን በፊትህ ቆመናል ወደ እኛ ተመልከት፤ እርዳንም። ብቸኛ መሪያችን አንተ ነህ ልቦቻችንን ከፍተህ ማደርያህ አድርግልን። ማድረግ ያለብንን ሁሉ አንተ አስተምረን፣ ሁላችንም በአንድ ላይ መከተል ያለብንን መንገድ አንተ አሳየን። እኛ ደካሞች እና ኃጢአተኞች ነንና፤ ሁከት እንዳናስፋፋ፣ አላዋቂነት ወደ ተሳሳተ ጎዳና እንዳይመራን፣ አድልዎ በድርጊቶቻችን ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድርብን እርዳን። ከእውነት መንገድ እንዳንስት፣ ወደ ዘለዓለማዊ እና ትክክል ወደሆነው ሕይወት አብረን እንጓዝ ዘንድ ከአንተ ብቻ የሆነውን የሕብረት መንፈስን ስጠን። ይህን ሁሉ በሁሉም ቦታ እና በሁሉም ሰዓት ከአብ እና ከወልድ ጋር አብረህ በሥራ ላይ የምትኖርን አንተን እንለምንሃለን፤ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም አሜን።**

## በምድር ላይ ከተሰጡን ስጦታዎች ሁሉ እውነተኛ ወዳጅ ምርጡ ነው።



ዘላቂ ወዳጅት በውስጡ ምንም ዓይነት የገንዘብና የጥቅም ጉዳይ የለበትም። ወዳችነት የሚመሰረተው በመሥዋዕትነትና በፍቅር መሠዊያ ላይ ነው። የጓደኝነት ዋጋው “ምን ማግኘት እችላለሁ?” የሚለው አሳብ ሳይሆን “በውስጡ ምን ዓይነት መልካም ነገር አለው?” የሚለው ነው።

ወዳጅነት የሀብት መሠረት እንጂ ሀብት የወዳጅነት መሠረት ሊሆን አይገባም።

በወዳጅነት ዙሪያ ብዙ ግጥሞችና ጽሑፎች ተጽፈዋል። ሶቅራጥስ “ከዓለም ሀብት ሁሉ የተሻለ ታማኝ ባልንጀራ ቢኖረኝ እወዳለሁ” ብሏል።

በመቀጠልም ምክሩን ሲለግስ “በጓደኝነት ውስጥ ለመግባት አትቸኩል ከገባህበት በኋላ ግን ሳታወላውል ቀጥ ባለ መልኩ ተጓዝ በማለት ይመክረናል”።

አርስቶትልም ስለ ጓደኛህ አያያዝ “እውነተኛ ወዳጅን በምትመለከትበት ዓይንህ ተመልከተው ራስህንም በምትይዝበት ሁኔታ ያዘው” ብሏል

ምንጭ - ስኬታማ የፍቅር ሕይወት (Successful Life of Love) በመምህር ዳንኤል ዓለሙ

ምሥጋና ካነበቡት ላካፈሉን! አቶ ፍቃደ አረዳ ( ወልቂጤ/እምድብር ሀገረስብከት )

**አብሮነት/ ተሳትፎ / ተልእኮ ለሲኖዶሳዊ ቤተክርስቲያንን**

# የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን የማህበራዊ እና ልማት ኮሚሽን በ256 ሚሊዮን ብር የልማት ሥራ ሊሰራ ነው








የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የማህበራዊ እና ልማት ኮሚሽን ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ከተባለ የአሜሪካ የተራዕዶ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች ውስጥ በሚገኙ ወረዳዎች ላይ ግብርናውን ያማከለ እና ለወጣቶች የሥራ ዕድል የሚከፍቱ የልማት ሥራዎችን ሊሰራ እንደሆነ ተነግሯል።

የማህበራዊ እና ልማት ኮሚሽኑ የገንዘብ ድጋፉን ያገኘው ማስተርካርድ ፋውንዴሽን የተባለው የአሜሪካ የእርዳታ ተቋም በአፍሪካ ደረጃ 'አፍሪካን ያንግ ዎርክስ ስትራቴጂ' የሚል መሪ ዕቅድ ቀርፆ፣ በአፍሪካ ደረጃ ወደ 30 ሚሊዮን የሥራ ዕድል ለወጣቶች ለመፍጠር እየሰራ ከሚገኝ ፋውንዴሽን ነው።

በዚህም መሰረት ከ30 ሚሊየኑ የአፍሪካ ኮታ በኢትዮጵያ ወደ 10 ሚሊዮን የሥራ ዕድል ለመፍጠር ከተለያዩ ተቋማት ጋር እየሰራ የሚገኝ እና ከነዚህም ተቋማት መካከል በሃገራችን ከሚገኘው የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት በኩል ነው የገንዘብ ድጋፉን መገኘቱ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ከስሙ ለመረዳት እንደሚቻለው በኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለውን ባህላዊ የግብርና አሰራር ለመቀየር እና በግብርና የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ለወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር በማስተርካርድ ፋውንዴሽን የሚደገፍ 'አደይ' (Agriculture-focused Dignified Employment for Youth in Ethiopia – ADEY) የሚባል የግብርና የሥራ ዕድል ፈጠራ ፕሮጀክት ቀርፆ እየሰራ ይገኛል።

በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ከማስተርካርድ ፋውንዴሽን ያገኘውን 70.5 ሚሊዮን ዶላር ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ በሁሉም ክልሎች ውስጥ ባሉ ከ350 በላይ ወረዳዎች ላይ በግብርናው ላይ ትኩረት አድርጎ ፕሮግራሙን ለአምስት ዓመታት ለመተግበር በማሰብ ከሥራው ስፋት እና ባህሪ አንፃር የተለያዩ ተቋማትን ለማሳተፍ እና ተቀናጅቶ ለመሥራት ስድስት ባለድርሻ አካላትን ከስሩ አቅፎ ፕግራሙን ተግባር ላይ ለማዋል ባቀደው መሰረት የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን የማህበራዊ እና ልማት ኮሚሽን የ256 ሚሊዮን ብር ጨረታውን በማሸነፍ ከተቋሙ ጋር ግንቦት 6 ቀን 2016 ዓ.ም. የውል ስምምነት ተፈራርሟል።

በዚህም መሰረት የልማት ኮሚሽኑ በአራት ክልሎች ውስጥ በሚገኙ አራት ሃገረስብከቶች ውስጥ ማለትም በጂማ-ቦንጋ ሃገረ ስብከት፣ በሆሳእና ሃገረስብከት፣ በሶዶ ሃገረስብከት እና በሃዋሳ ሃገረስብከት (በእምድብር ሃገረስብከት በከፊል) ውስጥ ለሚገኙ 61,193 ወጣቶች የሥራ እድል የሚከፍት ግብርና ተኮር የልማት ሥራዎችን በአምስት ዓመታት ውስጥ እንደሚሰራ ይጠበቃል።

## የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ትምህርት ሚኒስትር ...

ከገፅ 1 የዞረ

ክቡር ሚኒስትሩ ተቋሙን የጎበኙት የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ የምታበረክተውን ከፍተኛ አስተዋጽዖ እና ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ለማበረታታት እና ከዚህም በተሻለ መልኩ እንድትሰራ በትግበራው ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሟትን ተግዳሮቶች መቅረፍ በሚቻልባቸው እና ከመንግስት ጋር በትምህርት ዘርፍ ላይ አብሮ ለመሥራት የሚያስችሉ መንገዶች ላይ ተቀራርቦ ለመወያየት እንደሆነም ተገልጿል።

ብጹዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ በመርሃ ግብሩ ላይ ለክቡር ሚኒስትሩ እና ለእንግዶቹ ባደርጉት ገለፃ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያ የትምህርት ዘርፍ ላይ ያበረከተችውን እና እያበረከተች ያለውን አበርክትሆ አጠር ያለ ንግግር ካደረጉ በኋላ፥ የካቶሊክ ዩኒቨርሲቲ በርካታ ተማሪዎችን ተቀብሎ እንዳያሰለጥን እንቅፋት ከሆኑት ችግሮች ውስጥ ወደ ተቋሙ የሚወስደውን የመንገድ ችግር በማንሳት መንግስት አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርግ አሳስበዋል።

ክቡር ሚኒስትሩ ተቋሙ እየሰራቸው ያሉትን ሥራዎች ዞረው ከጎበኙ በኋላ ባደረጉት ንግግር መንግስት ተቋሙ ያሉባቸውን ችግሮች ለመቅረፍ የሚቻልባቸውን መንገዶች ለማመቻቸት ያላሰለሰ ጥረት እንደሚያደርጉ ቃል ገብተዋል።

የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የሆነው 'የቅዱስ ቶማስ አኪውነስ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ዩኒቨርሲቲ' ኢኳይስታ በአሁኑ ወቅት በሕክምና፣ በሜዲካል ላብራቶሪ ቴክኖሎጂ እና በሶሻል ዎርክ የትምህርት ዘርፎች 247 የሚሆኑ ተማሪዎችን ተቀብሎ እያሰለጠነ የሚገኝ ሲሆን፥ ወደፊት ከመንግስት ጋር ተቀራርቦ በመሥራት ከዚህ በተሻለ መልኩ የትምህርት ዘርፎችን በማስፋፋት በርካታ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር የአጭር ጊዜ ዕቅዶችን ቀርጾ እየሰራ እንደሚገኝም ተገልጿል።

ዩኒቨርሲቲው እስከ ዛሬ ድረስ ለዘጠኝ ጊዜያት ያህል ተማሪዎችን በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች አሰልጥኖ አስመርቋል።



## ... የ "Earth Day" አከበረ

ከገፅ 1 የዞረ

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የሶዶ ሀገረስብከት ማህበራዊ እና ልማት ማስተባበሪያ ጽ/ቤትም ዕለቱን ግንዛቤ በማስጨበጥ እና የተለያዩ ችግኞችን በመትከል አክብሯል።

በዕለቱም የቀድሞ የሶዶ ሀገሰስብከት ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ፀጋዬ ፣ የሀገረስብከቱ ሐዋርያዊ ሥራ አስተባባሪ ክቡር አባ ደጀኔ ሂዶቶ እና የማህበራዊ እና ልማት ጽ/ቤት አስተባባሪ አቶ ሙሉነህ ተስፋዬ ተገኝተዋል።

በመቀጠልም ብፁዕ አቡነ ፀጋዬ ለጽ/ቤት ሠራተኞች ምክር ለግሰዋል፤ በንግግራቸውም "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እኛ እንደመጣ እንዲሁም እግዚአብሔር ሁሉንም ፈጥሮ ሲጨርስ ሁሉንም እንድንንከባከብ ኃላፊነቱን ለኛ ሰጠ። ስለዚህም ለኛ የተሰጠንን ስንንከባከብ ትሩፋትን እናገኝበታለን። እኛም ዛሬ የሰማይና የምድርን መታረቅ እያሰብን ይህንንም ቀን እናከብራለን" ብለዋል።

ቀጥሎም ዕለቱን ለማሰብ የተዘጋጀው ችግኝ ተተክሎ በፀሎት ፕሮግራሙ ተጠናቋል።




**ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከሶሻል ሪሃብሊቴሽን ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው**

**"እግዚአብሔር በቃል ኪዳኗ ታቦት ኃይሉን በመግለጥ ዳጎንን ሰባብሮ እንደጣለው እንዲሁ እግዚአብሔር ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ በመወለድ በኃጢአት ምክንያት በእኛ ላይ ሠልጥኖ የነበረውን ሰይጣንን ድል ነሳው" (1ሳሙ.5፤6)**

# በፍትህና ሰላም ግንባታ ዙሪያ ለአመራር ኃላፊዎች ሥልጠና ተሰጠ



የቅዱስ ጳውሎስ የሕግ ታራሚዎች ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ ክፍል ከሰበካው ሰላምና ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ስር ለሚገኙ የማረሚያ ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች በአመራር እና በፍትህና ሰላም ግንባታ ዙርያ የሁለት ቀን ሥልጠና መስጠቱን ሻለቃ ፊጣ ቱሉ የክፍሉ ዋና አስተባባሪ ገለጹ።

መጋቢት 26 እና 27 ቀን 2016 ዓ/ም በአዲስ አበባ ካቶሊካዊ ሰበካ በቅዱስ ሚካኤል ሐዋርያዊና ማህበራዊ ሥልጠና ማዕከል በተሰጠው ሥልጠና ከፌደራል ማራሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ጽ/ቤት እና በሥሩ ከሚገኙ ከቃሊቲ፤ ከቂሊንጦ፤ እና ከገላን ማረሚያ ቤቶች ለተውጣጡ 55 ለሚሆኑ ከፍተኛ መኮንኖች፤ መስመራዊ መኮንኖች፤ ባለሌላ ማዕረጎችና ስቪል ሠራተኞች ሲሆን አባሎቹ በታራሚዎች ማነጽ እና ማስተዳደር ላይ የተመደቡና ከታራሚዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት ያላቸው ናቸው።

ሥልጠናውን በጸሎት የከፈቱት ክቡር አባ ተስፋዬ ወ/ማርያም የአዲስ አበባ ሰበካ ጠቅላይ ጽ/ቤት ኃላፊና እንደራሴ ሲሆኑ ክቡርነታቸው በሰጡት ሐዋርያዊ መመርያ ታራሚዎች ምንም እንኳን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ሕግን በመተላለፍ በፍርድ ቤት ትእዛዝ በማረሚያ ቤት ቢገቡም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ በመሆናቸው አቅም በፈቀደ መጠን የተሻለ እንክብካቤ አግኝተው፤ ለቀጣይ ሕይወታቸው የተሻለ የክህሎት ሥልጠና ተሰጥቷቸው፤ በሰሩት ድርጊት ተጸጽተው፤ የበደሉትን ሕብረተሰብ ለመካስ የሚያስላቸውን የመንፈስ ጽናት አግኝተው ለመውጣት እንዲችሉ የእናንተ እገዛ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በመግለጽ ሥልጠናውም የሚያተኩረው ባላችሁ ልምድና እውቀት ላይ የአመራር ብቃት ለማሳደግና በፍትህና ሰላም ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ታስቦ የተዘጋጀ መኖኑን ገልጸዋል። በመቀጠልም ሻለቃ ፊጣ ቱሉ የክፍሉ ዋና አስተባባሪ ይህ የታራሚዎች ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበርያ ክፍል ከተመሰረተ ከ1995 ዓ/ም ጀምሮ ላለፉት 21 አመታት በፌደራል እና በኦሮሚያ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ስር በሚገኙ ማረሚያ ቤቶች በመደበኛ ትምህርት፤ በሙያ ሥልጠና፤ በሕክምና ጤና አገልግሎት፤ በስነ-ልቦና የምክር አገልግሎት እና በሌሎችም በርካታ ሐዋርያዊ ሥራዎች መከናወናቸውን ገልጸው ይህ ዛሬ የተሰጠው ሥልጠና የዚሁ አካል መሆኑን አስረድተዋል።

በመቀጠልም አቶ ሰለሞን ደጀኔ የሰበካው የፍትህና ሰላም ቢሮ ኃላፊ የመሪነት ሚና ማሳደግ በሚቻልበት ዙሪያ፤ እና አንድ ክርስቲያናዊ መሪ ከታራሚዎች ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነት የካቶሊክ ቤተክርስቲያንን አስተምህሮ መሰረት ያደረገ ሥልጠና የሰጡ ሲሆን አቶ ወንዶሰን ከበደ ከባህር ዳር -ደሴ ሀገረ ስብከት በህንጸተ ሰላም ዙሪያ ለአመራር አባላት የፍትህና ሰላም ጽንሰ ሀሳብ ማወቅ አንድን መሪ ሙሉ ሊያደርግ የሚችል መሰረታዊ ክህሎት መሆኑን በምሳሌ የተደገፈ ትምህርት ሰጥተዋል።

በትምህርቱ ማጠቃለያ ብጹዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነ-የሱስ ሊቀ-ጳጳሳት ዘ-ካቶሊካውያን የኢትዮጵያ ካቶሊካውያን ጳጳሳት ጉባኤ ፕሬዝዳንት በመገኘት ለሥልጠናው ተሳታፊዎች በሰጡት ሐዋርያዊ መመሪያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን ለታራሚዎች የምትሰጠው አገልግሎት መሰረቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ገልጸው (ማቴ፤25,,31-46) ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኃልን? የሚለውን የጌታ ቃል መሰረት ያደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

በዚሁ መሰረት ብጹዕነታቸው የቅዱስ ጳውሎስ የሕግ ታራሚዎች ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል ተቋቁሞ ለታራሚዎች አገልግሎት እንድሰጥ ማድረጋቸውንና በዚሁ ክፍል አማካይነት በተለያዩ ጊዜያት ወደ ኦሮሚያ ማረሚያ ቤቶች በመሄድ በአዲስ አለም፤ በሸኖ፤በአዳማ ማረሚያ ቤቶች በመገኘት በማስተባበርያ ክፍሉ የተሰሩትን ለታራሚዎች አገልግሎት የሚሰጡትን መሰረተ ልማቶችን ማየታቸውን ገልጸዋል። እንድሁም በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ስር በሚገኘው ቃሊቲ ማረሚያ ቤት በተደጋጋሚ በመሄድ ታራሚዎችን እንደጠየቁና በዚህም ሞት የተፈረደባቸውን የቀድሞ የደርግ ባለስልጣናት ምህረት እንዲደረግላቸው ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ከሁሉም የቤተ እምነቶች አባቶች ጋር በመሆን ጥያቄያቸውን ለመንግሥት በማቅረብ በአመክሮ እንዲፈቱ መደረጉን አስረድተዋል።

የሥልጠናው ተሳታፊዎችም የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን በሁሉም ዘርፍ የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት የምታበረክተው አገልግሎት ከፍተኛ መሆኑን እንደሚያውቁ በመግለጽ ለተሰጣቸው ሥልጠና አመስግነው፤ ለወደፊትም ይህ ትብብርዋ በተለይም ለታራሚዎች የምትሰጠው አገልግሎት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የቅዱስ ጳውሎስ የሕግ ታራሚዎች ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበርያ ክፍል በኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን በአዲስ አበባ በለገሀር ካቶሊክ መድኃኔዓለም ቁምስና በቅዱስ ጁሰፔ ማዕከል ስም የተደራጁ የኢጣሊያ ኮሚኒቲ አባላት ጋር በመተባበር በኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ ዳለቲ ማረሚያ ቤት ለሚገኙ የሕግ ታራሚዎች አገልግሎት የሚሰጥ ግምቱ ብር 250,000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሸህ) በሆነ ወጪ አንድ የእህል ወፍጮ አስተክሎ መጋቢት 26 ቀን 2016 ዓ/ም በማህበሩ ተወካይ በአቶ አውሮ አማካይነት ለማረሚያ ቤቱ አስተዳደር ምክትል ኮሚሽነር አስረክቧል። የማህበሩ ኃላፊ ወ/ሮ አልሊያ ወደ ጣልያን ሀገር በመሄዳቸው አቶ አውሮ ማህበሩን በመወከል የእህል ወፍጮውን ከሐግቤስ አስመጪና ላኪ ድርጅት በመግዛት በራሳቸው ባለሙያ ወፍጮውን አስተክሎ ከማስረከቡም በላይ በብር 200.000.00 (ሁለት መቶ ሸህ )መድኃኒት በመግዛት ለዳለቲ ማረሚያ ቤት ማስረከባቸውን ሻለቃ ፊጣ ቱሉ የክፍሉ አስተባባር አክለው ገልጸዋል። ማስተባበርያ ክፍሉ ለተደረገው ድጋፍና ትብብር በታራሚዎች ስም ልባዊ ምስጋናውን ያቀርባል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ታራሚዎችን ማገዝ ለምትፈልጉ አዲስ አበባ ካቶሊካዊ ሰበካ ሐዋርያዊ አገልግሎት ጽ/ ቤት የቅዱስ ጳውሎስ የሕግ ታራሚዎች ሐዋርያዊ አገልግሎት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አካውንት ቁጥር 1000005060714 መሆኑን በትህትና እንገልጻለን።



# ኃይለ-ኢየሱስ (ወጣት በላይ) ማዕረገ ዲቁናን ተቀበለ

ሚያዝያ 12/2016 ዓ.ም በቫቲካን በቅዱስ ጴጥሮስ ቤተክርስቲያን ከተለያዩ 12 ሀገራት፤ ከተለያዩ ሰበካዎች ለተውጣጡ ለ19 ወጣቶች የዲቁና ማዕረግ በብፁዕ ካርዲናል አንቶኒዮ ታግል (Antonio Tagle - currently serving as the Pro-Prefect of Dicastery for Evangelization) ተሰጥቷል። በዕለቱም የሀረር ሀገረ - ስብከት ጳጳስ፥ ብጹዕ አቡነ አንጀሎ ፓጋኖ በተገኙበት፤ የሰበካቸው አገልጋይ ወጣት (መንፈሳዊ ልጃቸው) ን/ዲያቆን ኃይለ-ኢየሱስ/ ደርቤ በላይ ላቀው ከሌሎች አገልጋይ ወንድሞቹ ጋር የዲቁና ማዕረግን ተቀብሏል።

ብፁዕ አቡነ አንጀሎ ፓጋኖም በዕለቱ ከሀገረ ኢትዮጵያ በመነሳት በቫቲካን በቅድስት ቤተክርስቲያንን በአካል ተገኝተው ደስታውን በመካፈላቸው በዲያቆኑና በክቡራን ካህናት አባቶች በኩል ላቅ ያለ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

ዲቁናን የተቀበሉት ዲያቆናት የመጡበት ሀገር እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፤ ሲሪ-ላንካ (Siri Lanka 1)፤ ህንድ ( India =3 ዲያቆናት)፤ ናይጀሪያ - (Nigeria 1)፤ ኮሪያ (Korea = 2)፤ አንጎላ (Angola=1)፤ ኢትዮጵያ (Ethiopia =1)፤ ማዕከላዊ አፍሪካ (Central Africa =3 ዲያቆናት)፤ ካሜሮን (Camerun=1)፤ ቬትናም (Vietnam=1)፤ አንጎላ (Angola =2)፤ ጋና (Ghana =1) እና ቻይና (China = 2 ዲያቆናት) ናቸው።

*ምንጭ - ከማህበራዊ ሚዲያ*

# ማዕረገ ዲቁና የቅዱስ ፍራንቺስኮስ ታናናሽ ወንድሞች ማህበር

የቅዱስ ፍራንቺስኮስ ታናናሽ ወንድሞች ማህበር አባል የሆነው ወጣት ወንድማችን ወንድም ወልደ ገብርኤል (መልካሙ ወሌቦ) በአዲስ አበባ ሀገረ-ስብከት በሚገኘው በአስኮ፥ በቅዱስ ፍራንችስኮስ ገዳም/ቁምስና የዲቁና ማዕረግን ከብጹዕ አባታችን ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ እጅ ተቀብሏል።

*ምንጭ - ከማህበራዊ ሚዲያ*



**“ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካህን ይሆን ዘንድ በሰው እንዳልተመረጠ እንዲሁ ቅድስት ድንግል ማርያም የጌታ ማደሪያ ትሆን ዘንድ በእግዚአብሔር የተመረጠችና በመንፈስ ቅዱስ ለእርሱ ማደሪያነት የተዘጋጀች ናት” (የእስክንድርያው ዲዮናስዮስ)**

# የቫቲካን ሚዲያ ገጽ

ከመጋቢት 2016 ዓ. ም ዕትም የቀጠለ

## ክፍል ሁለት

# በጋብቻ ውስጥ ፍቅር አስፈላጊነት



### ፍቅር አይመካም

መታበይ የሚለው ቃል ከንቱ ውዳሴን፣ እብሪትን፣ ጉረኛነትንና መንጠባረርን ያመለክታል። ስለ ራሳቸው ብዙ ከማውራት መቆጠብን ብቻ ሳይሆን ፣ በሌሎች ላይ ማተኮርን የሚወዱ ሰዎች የትኩረት ምንጭ መሆን አያስፈልጋቸውም። ፍቅር አይታበይም የሚለው ተከታይ ቃልም ትርጉሙ ያው። በሌላ አነጋገር፣ በሌሎች ፊት ‹‹አንታበይም››። ከዚህ ሌላ ፣ መታበይ ጉረኝነትንና ከእውነታ መራቅንም ያሳያል። እነዚህን የመሰሉ ሰዎች ራሳቸውን ከሌሎች ይበልጥ ‹‹መንፈሳውያን›› ወይም ‹‹ጠቢባን›› አድርገው ስለሚያስቡ ከማንነታቸው በላይ ገዝፈው ለመታየት ይፈልጋሉ። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ግሥ በሌላ ወቅት ተጠቅሞ ሲናገር ‹‹እውቀት ያስታብያል፣ ፍቅር ግን ያንጻል›› (1 ቆሮ. 8፡1) ይላል። አንዳንዶች ከሌሎች የበለጠ እውቀት ስላላቸው ራሳቸውን ትልቅ አድርገው ያስባሉ፤ የሌሎች የበላይ ለመሆን ይፈልጋሉ። ሆኖም፣ እውነት ትልቅ የሚያደርገን የሌሎችን ሐሳብ የሚረዳ፣ ለሌሎች የሚያስብና ደካሞችን የሚያቅፍ ፍቅር። ቃሉ በሌላ ቦታም በራሳቸው መታበይ ‹‹የተወጠሩ›› (ንጽ. 1 ቆሮ. 4፡18) ነገር ግን በእውነተኛ የመንፈስ ‹‹ኃይል›› ሳይሆን፣ በባዶ ቃላት የተሞሉ ሰዎችን ለመውቀስ ጥቅም ላይ ውሎአል (ንጽ.1 ቆሮ. 4፡ 19)።

ክርስቲያኖች ስለ እምነት ያነሰ ዕውቀት ያላቸውን፣ ደካሞችን ወይም ስለ እምነታቸው ጥርጣሬ የገባቸው የቤተሰቦቻቸውን አባላት በመደገፍ ፍቅራቸውን ማሳየት ይገባቸዋል። አልፎ አልፎ የተገላቢጦሽ ሁኔታ ሊኖር ይችላል፤ በቤተሰብ ውስጥ አዋቂ ናቸው የሚባሉ ምእመናን ከመጠን በላይ ትምክህተኞች ይሆናሉ። በአንጻሩ ፣ ፍቅር በትህትና የሚገለጽ። ከልባችን ሌሎችን ለማወቅ፣ ይቅር ለማለትና ለማገልገል ከፈለግን፣ ትዕቢታችን ሊረግብና ትህትናችን ሊያድግ ይገባል። ኢየሱስ ሥልጣን በሰፈነበት ዓለም ውስጥ፣ እያንዳንዱ ሰው የሌላው የበላይ ለመሆን ይፍጨረጨራል፣ ‹‹በእናንተ መካከል ግን ይህ መሆን የለበትም›› (ማቴ. 20፡ 26) በማለት ለደቀ መዛሙርት ተናገረ። የክርስቲያናዊ ፍቅር ውስጣዊ አመክንዮ የታላቅነት ወይም የሥልጣን ጉዳይ አይደለም፤ ይልቁንም ‹‹ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን›› (ማቴ. 20፡ 27)። በቤተሰብ ሕይወት ውስጥ፣ ከሁሉ ዐዋቂ ወይም የበላይ የመሆን የፉክክር አመክንዮ ፍቅርን ያጠፋል። ስለዚህ፣ ‹‹ሁላችሁም እርስ በርስ በመከባበር ትሕትናን ልበሱ፣ ምክንያቱም፣ ‹እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል›› (1. ጴጥ. 5፡ 5) የሚለው የቅዱስ ጴጥሮስ ተግሳጽ ለቤተሰብም ይሠራል።

### ፍቅር ተገቢ ያልሆነ ነገር አያደርግም

መውደድ ጨዋና ለሌሎች አሳቢ መሆንም። ፍቅር ተገቢ ያልሆነ ነገር አያደርግም፣ወይም ብልግና የለበትም፣ ጨካኝ አይደለም። ድርጊቶቹ፣ ቃላቱና እንቅስቃሴዎቹ ደስ የሚያሰኙ ናቸው፤ ሻካራ ወይም ግትር አይደሉም። ፍቅር ሌሎችን ማሰቃየትን አጥብቆ ይጠላል። ይሉኝታ አንድን ሰው ‹‹አእምሮውንና ስሜቶቹን ማዳበርን፣ እንዲሁም እንዴት መስማት፣ መናገርና አንዳንዴም ዝም ማለት እንዳለበት መማርን የሚጠይቅ የስሜትና አድልዎ የሌለበት ትምህርት ቤት ነው››። ክርስቲያን ሰው በፈቃደኝነት የሚቀበለው ወይም የሚተወው ነገር አይደለም። ፍቅር መሠረታዊ ነገር እንደ መሆኑ መጠን ‹‹ማንኛውም ሰው በዙሪያው ካሉት ጋር ተስማምቶ የመኖር ግዴታ አለበት››። በየቀኑ ‹‹አንድ ሰው በሕይወታችን ውስጥ ቀድሞውኑ ሚና ቢኖረውም እንኳ፣ ወደ ሌላው ሰው ሕይወት ውስጥ መግባት፣ መተማመንንና መከባበርን የሚያድስ ስሜትንና መቆጠብን ይጠይቃል። በእርግጥ፣ የፍቅር ጥልቀቱ ሲጨምር፣ የሌላውን ሰው ነጻነት የማክበርና ሌላው ሰው የልቡን በር እስኪከፍት ድረስ የመጠበቅ ችሎታ በይበልጥ ማዳበርን ይጠይቃል››።

ከሌሎች ጋር በሐቅ ለመገናኘት ዝግጁ ለመሆን ‹‹ በጎ አስተሳሰብ›› አስፈላጊ። ይህም የራስን ችላ ብሎ የሌሎች ሰዎችን ድክመት ከመጠቆም አሉታዊ አስተሳሰብ ጋር አይጣጣምም። በጎ አስተሳሰብ ከራሳችን ውስንነቶች ባሻገር እንድንመለከትና ትዕግሥተኞችና ልዩነቶች ቢኖሩን እንኳ ከሌሎች ጋር እንድንተባበር ይረዳናል። በጎ አስተሳሰብ መስተጋብርን ይመሠርታል፣ ግንኙነቶችን ያዳብራል፣ አዳዲስ የውህደት መረቦችን ይዘረጋል፣ ጥብቅ ማኅበራዊ ትስስርን ይፈጥራል። በዚህ ዐይነት ይበልጥ እየጠነከረ ይሄዳል፤ ምክንያቱም፣ የባለቤትነት ስሜት ሳይኖር ለሌሎች ያለንን ቁርጠኝነት መቀጠል አንችልም፤ የራሳችንን ምቾት ብቻ በመሻት ላይ የምናተኩር ከሆነ የጋራ ሕይወት የማይቻል ይሆናል። ጸረ ኅብረተሰብ አkም ያላቸው ሰዎች ሌሎች ሰዎች ያሉት የራሳቸውን ፍላጎት ብቻ ለማርካት ነው ብለው ያስባሉ። በመሆኑም፣ ለፍቅራዊ ጨዋነትና ለመገለጫዎቹ ክፍት ቦታ አይኖርም። የሚወዱ ሰዎች የሚያስደስት፣ የሚያጸና፣ የሚያጽናናና የሚያበረታታ ቃል መናገር ይችላሉ። ‹‹ አይዞህ፣ ልጄ›› (ማቴ. 9፡2)፤ ‹‹እምነትሽ ታላቅ ነው›› (ማቴ. 15፡ 28)፤ ‹‹ተነሺ ቁሚ›› (ማር. 5፡ 41)፤ ‹‹በሰላም ሂጂ›› (ሉቃ. 7፡ 50)፤ ‹‹አይዞአችሁ፣ አትፍሩ›› (ማቴ. 14፡ 27) የሚሉ እነዚህ ቃላት ኢየሱስ ራሱ የተናገራቸው ናቸው። እነዚህ ሰውን የሚያዋርዱ፣ የሚያሳዝኑ፣ የሚያስቆጡ ወይም የሚንቁ ቃላት አይደሉም። በቤተሰቦቻችን ውስጥ፣ እርስ በርስ ስንነጋገር፣ ጨዋ ኢየሱስን መምሰልን መማር አለብን።

ይቀጥላል









ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከፍትህና ሰላም ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው።



በክቡር አባ አብነት አበበ
ዘማኅበረ ልኡካን/ ላዛሪስት

# መልካምን ለመሥራት እግዚአብሔርን መፍራት

ካለፈው ዕትም የቀጠለ (የመጨረሻ ክፍል)

## ጥበብን ፍለጋ

‹‹የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ›› (ምሳሌ. 1፡7) ከሆነ ጥበብ ማናት? ምንድን ናት? እንዴትስ ትገኛለች? የጥበብ ፍሬዎችና እሴቶች ምን ምን ናቸው?

**ጥበብ ማለት**

‹‹የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤ ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ››(ምሳሌ. 1፡7) እንደሚለው ጥበብ ማለት እውቀትን በትክክል መጠቀም ማለት። ማወቅ ማለት ጥበበኛ መሆን ማለት አይደለም፤ ጥበበኛ የሚያሰኘን እውቀትን በትክክለኛው መንገድ መጠቀም ስንችል።

ጥበብ ማለት ሕዝብን ለማስተዳደር (በትክክል ለመፍረድ) መልካሙንና ክፉውን መለየት የሚያስችል አስተዋይ ልቡና ማለት። (1ነገ 3፡9)።

**ጥበብን ለማግኘት**

መጽሐፍቅዱስእንደሚነግረንጥበብየሚገኘው ከእግዚአብሔር ሲሆን እርሱ ጥበብን የሚሰጠው ለሚጠይቁት ሰዎች። ‹‹ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል›› (ያዕ. 1፡5)። ጌታችን ኢየሱስ ‹‹ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ›› እንዳለው (ሉቃ. 11፡ 9) ጥበብን ማግኘት የምንችለው አምላካችንን ስንጠይቅ። ጥበብ እንዲህ ትላለች፡ ‹‹እኔ የሚወዱኝን እወድዳለሁ፣ ተግተው የሚሹኝም ያገኙኛል›› (ምሳሌ. 8፡17)።

**የጥበብ ፍሬዎች**

- ጥበብን የሚያገኙ የእግዚአብሔርን ወዳጅነት ያገኛሉ (ጥበ. 7፡14)።
- መልካም ምግባር፣ ቁጥብነትንና ጥንቁቅነትን፣ ፍትህንና ጽናትን ታስተምራለች (ጥበ.8፡7)።
- ሰው ያለፈውን እንዲያውቅ፣ መጪውንም እንዲተነብይ፣ ምሳሌዎችን እንዲተረጉም፣ እንቆቅልሾችንም እንዲፈታ፣ ምልክቱንና ድንቅ ነገሮችን የዓመታትና የዘመናትንም አመጣጥ እንዲያውቅ ታበቃለች (ጥበ. 8፡8)
- በብልጽግና ጊዜ አማካሪ ናት በችግርና በመከራ ጊዜ ደግሞ አጽናኝ ናት (ጥበ. 8፡9)
- ማመዛዘንና ማስተዋልን ትሰጣለች (ምሳ. 8፡5)
- ጥበብ ሲኖረን ክቡርና ቅን ነገርን እንናገራለን፣ ትክክለኛውን ነገር እንለያለን (ምሳ. 8፡6)
- እውነትን እንናገራለን (ምሳ.8፡7)
- ብልጽግናና ክብርን እንጎናጸፋለን (ምሳ. 8፡18)
- በመንገዳችን ተማምነን እንሄዳለን፣ እግራችንም አይሰናከልም (ምሳ. 3፡23)
- ስንተኛ የጣፈጠ እንቅልፍ እንተኛለን (ምሳ. 3፡24)
- ድንገት ከሚያስፈራ ነገር ከሚመጣውም ከኃጢአን ጥፋት አንፈራም (ምሳ. 3፡25)
- ጌታ መተማመኛችን ይሆናል (ምሳ. 3፡26)

**የጥበብ እሴቶች**

- ‹‹ጥበብ ከእንቁ ትበልጣለችና የከበረ ነገር ሁሉ አይተካከላትም›› (ምሳ. 8፡11)
- ጥበብ እንዲህ ትላለች ‹‹ፍሬዬ ከወርቅ ይበልጣል›› (ምሳ. 8፡19)
- ‹‹እኔን ያገኘ ሕይወትን ያገኛልና፣ ከጌታም ሞገስን ያገኛልና። እኔን ያጣ ግን ራሱን ይጎዳል፣ የሚጠሉኝ ሁሉ ሞትን ይወድዳሉ›› (ምሳ. 8፡35-36)።

እግዚአብሔርን በእውነተኛ ማንነቱ ስናውቀው እንወደዋለን፣ በቅዱስ ፍርሃት እንፈራዋለን፣ የሚገባውን ክብር እንሰጠዋለን፣ እንታዘዘዋለን፣ በመታዘዛችን ደግሞ በዚህ ምድር ደስታን በሚመጣውም ዓለም ዘላለማዊ ደስታን ይሰጠናል ስለዚህ ይህንን ሁሉ ማድረግ እንድንችል እግዚአብሔር አምላካችን ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች አንዱ የሆነው ጥበብን በመስጠት ይባርከን (1ቆሮ. 12፡8)። አሜን!

**ዋቢ ፡**

*Antonisamy, Fr. F. ‹‹An Introduction to Christian Spirituality.›› Bombay, St Pauls, 2008.*

*Stephen, Fr. George S.J. ‹‹Be Fruitful›› Reflections for a Week/Month Retreat. Bombay, St Pauls, 2003.*

*Wilson, Neil S. ‹‹The Handbook of Bible Application.›› USA, Tyndale house, 2000.*

# በአፋር ሰመራ - የልደታ ማርያም ዓመታዊ የንግስ በዓል በድምቀት ተከበረ

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ-ክርስቲያን በባህር ዳር - ደሴ ሀገረ-ስብከት፤ በአፋር በሰመራ ከተማ በሚገኘው የልደታ ማርያም ቅድስት ቤተክርስቲያንን ዓመታዊ ክብረ በዓል፤ የሀገረ ስብከቱ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ልሳነ ክርስቶስ ማቴዎስ፤ በኢትዮጵያ የቫቲካን አምባሳደር የቅድስት መንበር ተወካይ የሆኑት (ኑንሲዮ) ብጹዕ አቡነ አንቷን ካሚሌሪ እንዲሁም፤ የካፑቺን አባቶች፣ የቅድስት ማዘር ትሬዛ ገዳም እናቶች እና ምዕመናን፥ ከደሴ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን ቁምስና ምዕመናን እንግዶች፤ በኢትዮጵያ የCNEWA ዋና ኃላፊ ክቡር አቶ አርጋው፤ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች (IMCS) በተገኙበት ተከብሮ ውሏል።

በእለቱም በክቡር ቆሞስ አባ መብራቱ ትምህርታቸውን በሚገባ ተከታትለው ጨርሰው፥ ይህን ቀን በጉጉት ሲጠብቁ የነበሩት ሶስት ልጆች በቅድስት ቤተ-ክርስቲያን በብጹዕ አቡነ ልሳነ-ክርስቶስ አማካኝነት የመጀመሪያ ቅዱስ ቁርባን ተቀብለዋል።

ይህም ቀን የቫቲካን አምባሳደር ለመጀመሪያ ጊዜ የሰመራን ሐዋርያዊ አገልግሎት ከአቡነ ልሳኑ ክርስቶስ ጋር የጎበኙበት ቀን።

ከዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጋርም ተገናኝተው ሐዋርያዊ ምክር ሰጥተዋል።

ፎቶ፥ ክቡር ቆሞስ አባ መብራቱ።

*አዘጋጅና አቅራቢ፡- ባህር ዳር - ደሴ ሀገረ-ስብከት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ።*

# በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን በእምድብር ሀገረስብከት የሮር እና የመቃና ልደታ ለማርያም ዓመታዊ ክብረ በዓል በደማቅ ሁኔታ ተከብሮ ዋለ

በእምድብር ሀገረስብከት የሮር ልደታ ለማርያም ዓመታዊ ክብረ በዓል በዛሬው እለት ተከበረ። በዕለቱም መሥዋዕተ ቅዳሴ የመሩት እንዲሁም ቃለ እግዚአብሔርን ያካፈሉት የሀገረስብከቱ ተተኪ ጳጳስ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ናቸው። በቁምስናውም ለሀገረስብከታችን ተተኪ ጳጳስ ለሆኑት ለብፁዕ አቡነ ሉቃስ እንዲሁም ለብፁዕ አቡነ ሙሴ ሥጦታ አበርክተዋል።

በተመሳሳይ ዜና የመቃና ልደታ ለማርያምም ተከብሮ የዋለ ሲሆን መሥዋዕተ ቅዳሴን የመሩት የእምድብር ሀገረስብከት ጳጳስ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ሙሴ ገብረጊዮርጊስ ናቸው። የመቃና ቁምስና ለአቡነ ሙሴ ገብረጊዮርጊስ ከምዕመናን የምስጋና ስጦታ የተሰጣቸው ሲሆን በተጨማሪም ለቤተክርስቲያንኑ ደጀ ሰላም ስለሌለው አንድ በጎ ፈቃደኛ እናት 100,000 ብር ሰጥተው እንደሚያሰሩ ቃል ገብተዋል።

የእግዚአብሔር መንግሥት ይስፋ!

*ምንጭ፥ የእምድብር ሀገረስብከት ማኅበራዊ ተግባቦት ክፍል*

# በአዲስ አበባ ሀገረስብከት የሱባኤ እና የጸሎት ማዕከል ተመረቀ

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በአዲስ አበባ ካቶሊካዊ ሰበካ የመንፈሳዊ እና ሥነ ልቦና ሁለንተናዊ እድገት እና ጸሎት ቤት ግንቦት 03/2016 ዓ.ም የተመረቀ ሲሆን በቤተ ጥሞና ከራስ ፣ ከሌሎች፣ ከተፈጥሮ እና ከእግዚአብሔር ጋር ፈዋሽ ግንኙነቶችን በማዳበር የለውጥ ዕድሎችን በማቅረብ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ላይ የተመሰረተ፣ ሁሉም ግለሰቦች ለእግዚአብሔር ጥሪ በጸሎት እና በውስጣዊ ለውጥ ምላሽ መስጠት የማዕከሉ ተልዕኮ ነው።

በዕለቱም ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነ ኢየሱስ ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን ፣ ካህናት ፣ የቅድስት ሀና ደናግላን ገዳም እህቶች እንዲሁም ምዕምናን ተገኝተዋል።

ይህ ማዕከል በዋናነት ሰዎች ከራሳቸው ፣ ከአምላካቸው እና ከተፈጥሮ ጋር የፅሞና ጊዜ እንዲኖራቸው የሚያስችል ሲሆን ማዕከሉ ከእግዚአብሔር ፣ ከራስ እና ከሌሎች ጋር ያለንን ግንኙነት መሰረት በማድረግ መንፈሳዊ እና የስነልቦናዊ እገዛ ያደርጋል።

የቅድስት ሀና ልጆች ገዳም አባል ሲስተር ትዕግስት በርጋ " የጌታችን ትንሣኤ የእኛ የልጆቹ መንፈስ እንዲነቃቃ የሚያደርግ መለኮታዊ ኃይል። ወደ እግዚአብሔርም ልባችንን ፣ ራሳችንን ፣ መንፈሳችንን ማቅረብ የጥሪአችን አካል። ከራሳችን ጋር ግልፅ መስተጋብር ከሌለ ከሌሎች ጋርም ፍሬያማ መስተጋብር ማሳደር አይችልም እናም ዛሬ የሚመረቀው ይህ ማዕከል ወደእዚህ ለሚመጡት ሁሉ እግዚአብሔር ውስጣቸው ያስቀመጠውን ፀጋ በማግኘት እና መንፈሳዊነታቸውን የሚያስተጓጉሉ ነገሮችን የሚያፀዳ ማዕከል ነው። " ሲሉ ተናግረዋል።

የዕለቱን መስዋዕተ ቅዳሴ ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነ ኢየሱስ በዋናነት የመሩ ሲሆን የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈው "የተዘጋው የገነት በር ተከፍቶ ከእግዚአብሔር ጋር ስለታረቅን ደስ ይበላችሁ። ይህ ትልቅ ቦታ ጸሎት እንድናደርግ የተሰጠን። ምዕምናን ሱባኤ ለማድረግ በሩቅ ቦታ ይሔዱ ነበር አሁን ግን በእግዚአብሔር ፀጋ እና በረከት ይህ ቦታ ተመርቋል። ሕፃናት ፣ ወጣቶች እና ምዕምናን ወደእዚህ ቦታ መጥተው የሚጸልዩበት እና የምክር አገልግሎት የምናገኝበት ቦታ። በጸሎት ትልቅ መለኮታዊ ኃይል መንፈሳችንን እናድሳለን" ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል። መርኃግብሩም በጸሎት እና በቡራኬ ተጠናቋል።

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ሐዋርያዊ ሥራዎች ኮሚሽን ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**“እጠበኝ፣ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ፤”(መዝ.51፡9)**

# ቤተሰብ



በክቡር አቶ አርጋው ፋንቱ

# የፋሲካን ወራት መኖር በትኩረት

*የሥርዓተ-አምልኮ ወቅቶችን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት አስተንትነው፣ ጸልየውና ተጋድለው ላስቀመጡልን ቅዱሳን አባቶች ምስጋና ይግባቸውና በጥልቀት ብናስብ፣ ብናስተነትንና ብንኖርበት እንዴት ያሉ አስደማሚና አስደናቂ ወቅቶች ናቸው?*



የአርባ ፆም ወቅትን፣ በፆም፣ በጸሎትና በበጎ ተግባር ተጋድሎ ኖረን የጌታችንን ትንሣኤ (ፋሲካን) አከበርን። የእምነታችን ዋነኛ አምድና ምሰሶ አገኘን። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳስተማረንም "ክርስቶስ ከሙታን ባይነሳ ኖሮ፣ እምነታችን ከንቱ በሆነ ነበር። "(ንጽ. 1ቆሮ.15፡14)። እውነትም ነው። ይህንን የእምነታችንን አምድ አጥብቀን መያዛችን ሊያስደስተን ይገባል። በዚህ ደስታ ውስጥ ሆነን ነው ከፆም ወደ መፈሰክ፣ ከጸሎት ወደ ዘና ማለት፣ ከበጎ ተግባር ላላ ወደ ማለት የተሸጋገርን የሚመስለን። በአንድ መልኩ ሲታይ አዎ! ሞትን ድል ነስቶ የተነሣው ጌታ የሰጠን የደህንነት ደስታ ቀላል እንደማይሆን። ሆኖም ግን አርባ ቀናትን ባሳለፍንበት ሁኔታ ሳይሆን ለየት ባለ መልኩ ደግሞ ከጌታችን ትንሣኤ እስከ የጳራቅሊጦስ በዓል ድረስ ያሉትን ሃምሳ ቀናት የምናሳልፍበትን ሁኔታ እንቃኝ። እንደ ሥርዓተ-አምልኮአችን ቀመር ከትንሣኤ በዓል ቀጥሎ ያለው እሑድ ዳግም ትንሣኤ፣ ቀጥሎ ያለው እሑድ የኤማሁስ መንገደኞች፣ ቀጥሎ ባለው እሑድ የኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ መገለጥ(ሁለት እሑዶች)፣ ቀጥሎም ለጴጥሮስ የተሰጠው የእረኝነት ኃላፊነት፣ በአርባኛው ቀን እርገት፡ ከዚያም የመንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ የመውረድ በዓል - የጳራቅሊጦስ በዓል - በታላቅ ድምቀት ይከበራል። እነዚህ ጊዜያት በአብዛኛው በደስታና ዘና በማለት የታጀቡ ይመስላሉ።

በቤተክርስቲያንን አካባቢ የምናያቸው በተለይም በመንበረ ታቦት አካባቢ የምናያቸው አልባሳት (የካህናትን ልብሰ-ተክህኖ ጨምሮ) በነጭ የታጀቡ ናቸው። እንደ የቤተክርስቲያንን አስተምህሮ ነጭ ቀለም ደስታን፣ ንፅህናን እና ክብርን ይወክላል። የክርስቶስ ትንሣኤ የደስታችን ምንጭ መሆኑ፣ የክርስቶስ ትንሣኤ ደስታ ተካፋዮች ለመሆን በአርባ ፆም ወቅት ያሳለፍነው የፆም፣ የጸሎትና የተጋድሎ ተግባራት፣ ወደ ኋላ ላለመመለስ ወይም ከቀድሞ ያልፀዳ ሕይወታችን ለመላቀቅ በንስሐ ታጥበን በፀዳ መንፈስና አስተሳሰብ የትንሣኤው ደስታ ተካፋዮች ለመሆን መቅረባችንና በዚያም ለመቀጠል መወሰናችን ማሳያ ነው። ዘማሪው ዳዊትም "እጠበኝ፣ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ፤"(መዝ.51፡ 9) በማለት ነፅቶ የመቅረብን ፋይዳ ይነግረናል። የትንሣኤው ጌታ በክብር ዙፋኑ ላይ ለመሆኑ የመታደም ክብርም ነው። ራዕየ ዮሐንስም "ታላቅና ነጭ ዙፋን፡ በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፤"(ራዕ.20፡11) በማለት የክብሩ ሥፍራ ምን መልክ እንዳለው ይነግረናል። የአሁኑ ዘመን ባያዥጎረጉረውም ነጭ ልብስ (በተለይም ነጭ ነጠላ) ለብሶ ወደ ቤተክርስቲያንን መሄድ የኢትዮጵያውያን ልዩ መገለጫና የእምነት ንፅህና አስተምህሮ ውጤት እንደሆነ ይታመናል። ነጭ ለብሶ ወደ ቤተክርስቲያንን መሄድ ለመንፃትም ቃል የመግባት ምልክት ነው። የቀለሙን ጉዳይ እግረ መንገዴን አነሳሁት እንጂ ዋናው ሀሳብ የየጊዜያቱ ክስተቶች ለክርስቲያናዊ ሕይወታችንና በእምነታችን ጠንክረን ለመኖር ያላቸውን ፋይዳ በትንሹ መቃኘት።

ምንም እንኳን የትንሣኤው ክስተትና ድባብ የደስታ፣ የንፅህናና የክብር መገለጫ ቢሆንም እንደ ሰብአዊ ፍጡር እና እንደ ክርስቲያን ስንኖር ከትንሣኤ እሑድ እስከ የጳራቅሊጦስ በዓል ድረስ ያሉት የሥርዓተ-አምልኮ ንባባትና መልዕክቶች የውስንነቶቻችንና የደካማነታችን ማሳያዎችና መቀስቀሻዎች ናቸው።

በዳግም ትንሣኤ ዕለት የቶማስ በሥፍራው አለመኖር የእምነታችን ተጠራጣሪነት አንዱ ማሳያ ነው። በዚህ ዘመንና በየቤታችን ስንቶች ቶማሶች እንኖር ይሆን ብለን ራሳችንን መጠየቁ መልካም ነው። ትልቁ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ማሳያ ምላሽ "ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው"(ዮሐ.20፡ 29) ያለው ዘመን ተሻጋሪ ሆኖ ወደኛ ዘመን የደረሰው የእምነት የምሥራች ቃል ነው። ከመደሰታችን ጎን በአእምሮአችንም ሆነ በዓይናችን ውልብ ከሚልብን የእምነት ጥርጣሬ ለመራቅ የፋሲካን ወራት በትኩረት ለመኖር መታገልን አንድ ማለትን ይጠይቃል። የትንሣኤውን ደስታ ከማጣጣም ጎን ደግሞ እንደ የኤማሁስ መንገደኞች ግራ መጋባትና እያየን ማየት አለመቻላችን አንዱ የዘመናችን በእምነት የመኖር ፈተና ነው። በመሆኑም እርሱ እንጀራውን ሲቆርስ ዓይናቸው እንደተገለጠ ሁሉ፣ እኛም በፋሲካ ወራትም ሆነ በተሰጠን የእምነት ዘመናችን ስንኖር ሁልጊዜ ዓይናችን ይገለጥ ዘንድ፣ ከጥርጣሬውና ከግራ መጋባት ርቀን ለመኖር ሳናቋርጥ ወደ የክርስቶስ ማዕድ (ቅዱስ ቁርባን) መቅረብና እርሱን ወደ ውስጣችን ከማስገባት አለመቦዘን። ወደ ማዕዱ እንዳንቀርብና ዓይናችን እንዳይገለጥ የሚያደርጉን እጅግ በርካታ ነገሮች ባሉበት ዘመን መኖራችንንም አንዘንጋ።

ሐዋርያቱ ግራ ተጋብተውና በፍርሃት ተውጠው፣ በራቸውን ዘግተው በተቀመጡበት ሥፍራ ሁሉ በመሃላቸው በመገኘት "ሰላም ለናንተ ይሁን፡"(ሉቃ.24፡36) ያለው የትንሣኤው ጌታ ዛሬም ለቃሉ ታማኝ ነውና፡ "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው አለሁና።" (ማቴ.18፡ 20) ያለውን ቃል እንደሚያፀና በማመን፣ ከስጋታችንና ከጥርጣሬአችን ለመራቅ፣ በእምነትም ለመጽናት፣ ለሌሎችም በረከት ለመሆን ሁልጊዜ እንደቤተሰብ በጸሎት ከመትጋት አለማቋረጥን በመለማመድ የፋሲካን ወራት የትኩረት ሕይወት የአኗኗራችን መርህ እናድርገው።

ሐዋርያቱ ተስፋ ቆርጠው ወደ ቀድሞ ሕይወታቸው በመመለስ ዓሣ ማጥመድ ሥራ ላይ ተሰማሩ። ሕይወትን እናሸንፋለን ብለው በሌሊት በብርድና በውርጭ ውስጥ ሆነው መረባቸውን ቢጥሉም፡ እርሱ የበረከቱ ጌታ ከነርሱ ጋር አልነበረምና መረባቸው ባዶ ሆኖ ተስፋ ወደመቁረጡ ተቃርበው ነበር። ነገር ግን ቦታና ሁኔታ የማይገድበው የትንሣኤው ጌታ በአጠገባቸው ተከስቶ የጠየቃቸው ስለ ዓሣ አለማጥመዳቸው ሳይሆን ሆዳቸውን ከመሙላት ፍላጎት ጋር የተያያዘውን ጥያቄ፡ "ልጆች ሆይ! አንዳች የሚበላ ነገር አላችሁን?" (ዮሐ.21፡5) በማለት ነበር። ተስፋ የቆረጡት ዓሣ አጥማጆች ምላሽም "የለንም" የሚል የድካም ምላሽ ነበር። እርሱ የሌለበት፣ ከርሱ የራቀ ሕይወት ቋቱ ጠብ የማይል መሆኑን ከሐዋርያቱ ገጠመኝ መረዳት ይቻላልና የፋሲካ ወራት ሕይወታችን ተሞክሮ ለከንቱ ልፋት እንዳይሆን ትኩረትን እንጨምርበት ዘንድ ያሳስበናል። በቀጣዩ እስክንገናኝ ይህን አስተነትነዋ ለፍሬ ያርግልን። አሜን።

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና ከጤና ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው



በክቡር አባ ፊሊጶስ ደንድር
የእምድብር ሃገረስብከት ካህን

# “ወደ ተቀደሰች ተራራ ሊወጣ የሚችል ማን ነው እርሱ ትሑት ልብ ያለው ትዕዛዙን የሚጠብቅ”

## [መዝ. 24 ፤3]

*ወደ ተቀደሰች ተራራ ሊወጣ የሚችል ማነው ሲል ይህች የተቀደሰች ተራራ የእግዚአብሔር መኖርያ ስትሆን ይህችን ተራራ ሊያይ የሚችል ሰው በክፋት የተሞላ የሆነ ሳይሆን ትሑትና የዋህ የሆነ ሰው። ትሑታን የሆኑ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕግ የሕይወታቸው መተዳደሪያ ደንብ አድርገው ይቀበላሉ። ሕጉም ይመራቸዋል፣ ያፀናቸዋል፣ ያስተሳሥራቸዋል፣ ያፋቅራቸዋል ወዘተ.....*

የዋህ የሚያመለክተውም ከሰው ጋር ባለን ግንኙነት የምናሳየውን አክብሮት ብቻ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ፊት በተሰበረ ልብና በትህትና መቅረብ። የዋህ ሲባል ምንም የማያውቅ፣ ምስኪን፣ ጅል ወይም ዝምተኛ ማለት ነው ብለው የሚተረጉሙ ብዙዎች አሉና ይህ የተሳሳተ ዕይታ። የዋህ ሲባል ልቡ እውነትን እያወቀ ቢበድሉትም ለእግዚአብሔር ክብር ብሎ ሁሉን ነገር አሳልፎ የሚሰጥ። ራሳቸውን በመግዛት በፍቅር የሚኖሩ ሕይወታቸው በሙሉ ለፍቅር አሳልፈው የሰጡና ለፍቅር የሚገዙ ናቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላቲያ ክርስቲያኖች ስለ መንፈስ ቅዱስ ፍሬ ሲያስተምራቸው “የዋህነት” ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች አንዱ አንደሆነና (ገላ 5፣22) መንፈስ ቅዱስ አምላክ ከሚለግሳቸው ፍሬዎች አንዱ የዋህነት ነው የዋህ መሆን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ። መንፈስቅዱስን በውስጣችን እንዲሠራ ካልጋበዝነው ፍሬውን ለማግኘት ያስቸግራል። የዋህነት ራስን በማታለል የሚገኝ ሳይሆን ራስን በመግዛት የሚገኝ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። ራሳቸው ለአምላካቸው አስገዝተው የሚኖሩ ሰዎችና የፈጣሪን ፈቃድ በማስቀደም የሚኖሩ ሰዎች የዋሃን ይባላሉ።

“እንደ እባብ ብልሆች እንደ እርግብ የዋሆች ሁኑ” የእባብ ባህሪያትን እርግብ ልትወስድ አትችልም። የእርግብ ተፈጥሮ የዋህነት ሲሆን የእባብ ደግሞ ብልህነት። የዋህነት ምድርን ለመውረስ የሚያስችል ኃይል ያለው እንጂ ብልህና መርዛማ እንደሆነው እባብ ተምሳሌት አይደለም ይልቁንም ሰውኛ ዘይቤን የተጠቀመው ልክ እንደ እርግብ የዋህ ሆኖ መኖር ለምስጉንነት ተመራጫ ሆኖ የሚቀርብ ስለሆነ። እርግብ በኖህ የጥፋት ዘመን ከዳኑት አእዕዋፍት መካከል እንዷ ስትሆን የጥፋት ዘመን ማብቃቱን አለማብቃቱን ለማረጋገጥ ተልካ በአፏ የለመለመ የወይራ ቅጠል ይዛ የተመለሰች የሰላም መልእክተኛ ስትሆን (ዘፍ 8፤11) እባብ ደግሞ በኦሪት ዘመን እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ልጆች ጋር በማለያየት የጥልን ግድግዳ ያቆመና ራሱን እንደ አዋቂ የሚቆጥር አሳሳች እና በተንኮለኛነቱ እግዚአብሔር የረገመውና በደረቱ እንዲሳብ የተፈረደበት እንስሳ ነው (ዘፍ 3፡1)።

የዋሆች ሲባሉ እግዝአብሔርን የሚያስደስት ልብ ያላቸው ልባቸው የተገራና ያልደነደኑትን ነው (ያቆ3፣7)። የዋሆች አንደበታቸውን ያረሙና ከንግግራቸው መልካም ፍሬ የሚለቅሙ ጣፋጭ ንግግር የሚናገሩ ንግግራቸውም እግዚአብሔር የሚያስደስት። ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ውስጥ ራስን መግዛት (ገላ 5፣22) አንዱ ሲሆን ዋናው የየዋሆች መገለጫ ደግሞ ራስን መግዛት።

እግዚአብሔር ሳሙኤልን ከእሴይ ልጆች መካከል ንጉሥ የሚሆን ሄደህ ቀባ ባለው ጊዜ በመጀመሪያ ሊቀባ የፈለገው የአቢኤል ልጅ ነበር እርሱ ከሁሉም ግዙፍ ነበረ ነገር ግን እግዚአብሔር ልብን እንጂ ፊትን አያይምና ከሰባቱ ልጆች የመጨረሻውን ዳዊትን መረጠ ምክንያቱም ዳዊት ልቡ ንፁህና ትሑት ቅን ልብ ያለውና የይቅርታም ሰው ነበር።

ዳዊት የተቀባና ኃያል ቢሆንም ቂም በቀል የሚያውቅ አልነበረም ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ያላደረገ ውጥረት አልነበረም ዳዊት ግን ይህን ቢያውቅም ብዙ ምቹ ጊዜ አግኝቶ ሳኦልን ለመግደል ቢችልም እንኳን እግዚአብሔርን የሚፈራና የይቅርታ ልብ ስለነበረው እግዚአብሔር የቀባውን አልገድልም በማለት በርህራሄ በማየት ትቶታል (1ሳሙ 9፣1-7)

የዋህነት ከትሕትና ጋር ይዛመዳል ተቃራኒው ደግሞ ትዕቢት። ሁለንተናውን ለእግዚአ ብሔር የሰጠ እግዚአብሔር ይጠቀምበታል። ስለ መብቱ የማይከራከር ሌላው ሲሳካለት እንደራሱ የሚቆጥር ሌላው ሲያዝን የሚያዝን ሌላው ሲቸገር በማዘን የሚረዳና ስህተቱን የማይሸፍን ሰው በየዋህነት መስፈርት ይጠቃለላል።

ክርስቲያን ሆኖ መኖር እንደ ጅልነት በሚቆጠርበት ዘመን የዋህ ሆኖ መኖር ሳይከብድ የሚቀር አይመስለኝም ነገር ግን የተራራው ስብከት በየዋህነት መኖር ለበረከታችን እንደሚጋብዝ ያስተምረናል። ጲላጦስ ክርስቶስ የገሊላ ሰው መሆኑን ጠይቆ በተረዳ ጊዜ ከሄሮድስ ግዛት እንደሆነ በተገነዘበ ሰዓት ወደ ሄሮድስ ስደደው ሄሮድስም እየሱስን ለማየት ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ምኞት ስለነበረው ባገኘውም ሰዓት ብዙ ጥያቄ ጠየቀው ነገር ግን ክርስቶስ ኃይል እያለው ጥበብ እያለው አምላክ ሆኖ ሳለ በተራ ገዥ ፊት ቆሞ መልስ እንኳን ሳይሰጥ በየዋህነትና በትህትና መቆሙ (ሉቃ23፣8-9) የየዋህነት ፍፁም ተምሳሌት።

### የዋህነት በመስቀል ይመሰላል

መስቀል ለክርስቲያኖች ቤዛቸው መመኪያቸው። የክርስትና ጉዞ የመስቀል ጉዞ። መስቀል ክርስቲያኖች ከነበሩበት የጨለማ ጉዞ ወጥተው አዲስ ጮራ ያዩበት የሕይወት ትልቁ ገፅታ። ክርስቶስ ራሱን አሳልፎ በመስጠት የፍቅርን እውነተኛ ትርጉም የገለጠው በመስቀል። መስቀል አምላክ ለፍጡራን የምህረት እጆቹን የዘረጋበት ምልክት። ክርስቶስ ራሱን በማዋረድ ሌሎችን ከፍ ለማድረግ ሲል የመጨረሻ ውርደትን ተከናንቦ እንደ ሚጎተት በግ በመጎተቱና በመስቀል ላይ በመቸንከር መሞቱ ምን ያህል የየዋህነት ተምሳሌት መሆኑንን መመስከር ይቻላል። እርሱ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ሐሳብ ለመፈፀም እስከ መስቀል ሞት የታዘዘ ነው በዚህም ምክንያት እግዚእብሔር አብ ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው ከስምም በላይ የሆነ ስም ሰጠው (ፊሊ. 2፣6-10) የዋህነት መስቀል ነው ያልኩት ዋነኛው ምክንያት ራስን ማዋረድ፣ ባዶ ማድረግ፣ ራስን መካድ፣ መስቀሉን መሸከምና ክርስቶስን መከተል ከባድ ፈተና በመሆኑ የዋህ እና ትሁት ካልሆንን በስተቀር ይህንን ማለፍ ስለ ማይቻል።

### የዋህነት የሰማያዊ ቤት መግቢያ ቁልፍ ተምሳሌት

በመንግስተ ሰማይ አደባባይ ላይ ቆሞ በር እንዲከፈትለት የሚፈልግ ሰው ቁልፉ የዋህነቱ ነው። ትሕትና የመንግስተ ሰማይ መክፈቻ ቁልፍ። ትሕትናን እንደ ልብስ ያልለበሰ ሰው የመንግስተ ሰማይ ደጃፍ ለመቆም የሚያስችል ቲኬት አልቆረጠም ማለት።

የዋሆች የመንግስተ ሰማይ መግቢያና መውጫ ቁልፍ ስላላቸው እግዚአብሔርን ይመለከቱታል። የዋህነት የነፍሳት ማረፊያ ወደብ። በዘላለማዊ ቤት ለማረፍ ከሚያስፈልጉን መሠረታዊ ነገሮች አንዱ የዋህነት። የዋህነት የወንጌል ትዕዛዝ። በየዋህነት የሚኖር ነፍስ የሰከነ ልብ ይኖረዋል ያልደነደነ ልባዊ ማንነትን ይላበሳል። በመንግስተ ሰማይም ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል።

### የዋህነት የክርስቲያን መታወቂያ ካርድ ተምሳሌት

የክርስቶስ ዋናው መታወቂያው ራሱን ትሑትና የዋህ በማድረግ ወደ ምድር መምጣቱና እራሱን መስዋዕት ማድረጉ። ትሕትናን ተከትሎ የሚመጣው ትዕግስት። ትሕትናን የተላበሰ ሰው ነገሮችን በትግስት የማለፍ ብቃት አለው። ክርስቶስም በመቻል በትዕግስት አሸንፎአል። (ማቴ 27፣26-40) የዋሆች ፈተናዎችን በትግስት ተቋቁመው የሚኖሩበት ሃይል የሚያገኙት ከልዑል እግዚአብሔር። የኢዮብን ታሪክ ብንመለከት ሰውነቱ እስኪተላ ያ ሁሉ ሰቆቃ ሲደርስበት እግዚአብሔርን አልካደውም ያለ ታላቅና ቅዱስ ሰው። (ኢዮ 7፣5) ሰዎች በተለያዩ የሙያ ዘርፍ ተሰማርተው ሲሰሩ የራሳቸው የሆነ መለያ አላቸው መታወቂያው የዋህነቱና ትሕትናው። የዋህነትና ትሕትና የክርስቲያን መታወቂያ ካርድ ናቸው።“ክርስቶስ በቅዱስ ቃሉ ሲናገር እኔ በልብ የዋህና ትሁት ነኝ ይላል” (ማቴ 11.29)ክርስቶስ የዋህ እንደሆነ እኛም የዋሆች ልንሆን ይገባል።

### ትሕትና መስዋዕትነት ነው

ነብዩ ሚኪያስ “ወደ እግዚአብሔር ቤት ምን ይዤ ልቅረብ ይልና ጠቦት፣ ፍየል፣ ዘይት ወይስ የበኩር ልጄን ባለ ጊዜ አይ ሰው ሆይ የሚያስፈልገውን” እግዚአብሔር እርሱ ነግሮሃል ከአምላክህ ከእግዚአብሔር ጋር በትሕትና ተጓዝ” ሚኪ6፣6 ይህ ነብይ በትሕትና ተጓዝ ሲል እግዚአብሔር ምንም እንኳን የማይዳስስ፣ የማይጨበጥ፣ የማይወሰን ቢሆንም በትሕትና መጓዝ ያለብን ቃሉን አክብረን በቃሉ ስንኖርና ቃሉ የሕይወታችን መሪ አድርገን ስንኖር መሆኑን። ትሕትና መስዋዕትነት ነው ሲባል የተአዝዞና የእግዚአብሔርን ፍቃድ ይሁን ብሎ የመቀበል ነው ማለት። የእግዚአብሔርን ፍቃድ ያላስቀደሙ ሰዎች እጣ ፈንታቸው ከእግዚአብሔር ጥበቃ መራቅ ሲሆን ቅጣት እንደሚደርሰባቸውም ግልፅ ነው እንደ ምሳሌ ብንወስድ በኦሪት ዘመን በውሃ ጥፋት የጠፉትን ማስታወስና ማስተዋል እንችላለን። በተዓዝዞና የእግዚእብሔርን ህግ በመጠበቅና በማስቀደም የኖሩትን እግዚአብሔር ሕይወታቸውን እንደባረከና የተትረፍረፈ ሕይወት እንደሰጣቸው ማየት ይቻላል። እንደ ምሳሌ አብርሃምን፣ ሙሴን፣ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ማንሳት እንችላለን። ዳዊት በመዝሙሩ እግዚአብሔር ከኛ የተሰበረ ትሑት የተገራ ልብ እንደሚፈልግ (መዝ50፣17) ሰዎች የተሰበረ ልብ ሊኖራቸው እንደሚገባ ያስረዳል። ይህ ካልሆነ ግን የደነደነ ልብ ለይቅርታና ለምህረት እንደ ማይሆንና እንኳን እግዚአብሔርን ማየት ቀርቶ አጠገባቸውን ያለውን ባልንጀራቸውን ለማየት የተጋረደ መጋረጃ እንደሚሆንባቸው ያስረዳል። አንዳንዴ ሰዎች እውነትን እያወቁ ግብዝ የሚሆኑ፣ የእኔ ትክክል ነው የሚሉ ብዙ ይገኛሉ። ብዙዎች ደግሞ አብዛኛው ሰው ስለደገፋቸው ብቻ እውነትን የተናገሩ ስለእውነት የፈረዱ፣ እውነትን ያስተማሩ ይመስላቸዋል እንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች በየዋሆች መዝገብ የማይሰፍሩ ናቸው። የዋሆች እውነትን እየተረዱ ለማውጣትና ትክክል ነው ለማለት ይከብዳቸዋል ሲበደሉም ስለ መብታቸው አይከራከሩም፣ ፍትሕ ሲጓደልባቸው እግዚአብሔር ብቻ ዳኛ እንደሆነ በማወቅ ሁለንተናቸው ለእግዚአብሔር በመስጠት ይኖራሉ የዋህነት መገለጫቸው ነው እንደዚህ ዓይነት ሰዎች የዋሆችና ትሑቶች ተብለው ይጠራሉ።

የእኛም የክርስቲያኖች ሕይወት ክርስቶስ እንዳስተማረው ዓይነት ማለትም የየዋህነትና የትሕትና መንፈስ መላበስ እንዳለበት ይነግራል። እንደ መጥምቁ ዮሐንስ እራሳችንን ትሁት በማድረግ በማውረድ እኔ የክርስቶስን የጫማ ክር መፍታት የማልችል ሰው ነኝ በማለት እራሳችንን ዝቅ ማድረግ ይኖርብናል። ዮሐንስ መጥመቅ የዋህ፣ የፍቅር፣ የትሕትና መንፈስ የተላበሰ ቅዱስ ሰው በመሆኑ ክርስቶስ እርሱን ከፍ በማድረግ በዚህች ምድር ዮሐንስን የሚያክል ትልቅ ሰው እንደሌለ በቅዱስ ቃሉ አስቀምጦአል። ክርስቶስም ያ ሁሉ በደል ሲደርስበት “የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው” ብሎ ወደ አባቱ መማፀኑን (ማቴ 23፣34) ይህ የየዋሆች የበደል መልስ መሆኑን አስተምሮናል።

# የጥሪ ማዕድ

## የሕክምና ተልዕኮ እህቶች ማኅበር
## Medical Mission Sisters

*Called to be a healing presence at the heart of a wounded world*

**“ብርሃናችሁ በዓለም ሁሉ ይብራ”** ማቴ. 5: 16

**“let your light shine”** Mt. 5 - 16



ማህበራችን እ.ኤ.አ በ1925 በሲስተር አና ደንግል (ዶር) Sister Anna Dengel (Dr.) በአሜሪካ ተመሠረተ

**የማህበራችን ዋነኛው ዓላማ -** የክርስቶስን የማዳን ሥራ አገልግሎት በሕክምናና በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ።

**መስፈርታችን -**

- **በቅድሚያ ሕይወቷን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎትና ለድሆች መስጠት የምትፈልግ**
- **ለጸሎትና ለእግዚአብሔር ትልቅ ስፍራ ያላት**
- **በዓለም አቀፍ ማኅበር መኖርና ማገልገል የምትፈልግ**
- **የትምህርት ደረጃ 10+2 እና ከዚያም በላይ**

ቦሌ ጌስት ሃውስ አካባቢ
ቤት ቁጥር - 68
አድራሻችን አዲስ አበባ / ቂርቆስ - ወርዳ 01

የስልክ ቁጥር 0911055968 / 0911400139 / 0911106561 / 0923241466

ፖ.ሣ. ቁጥር 2891

| | |
|---|---|
| አድራሻችን | ወልቂጤ ጉራጌ |
| ስልክ ቁጥር | 011 3 30 52 37 |
| | ሲስተር ንግሥት ብሩ |
| ፖ.ሣ. ቁጥር | 11 |

## የኮንሰላታ ማርያም ልውካን እህቶች እና አባቶች ገዳም

“የኮንሰላታ የአጽናኝቷ ማርያም ልውካን እህቶች እና አባቶች ገዳም ዓለም አቀፍ ተልዕኮ ያለው ሲሆን የገዳማችን ልዩ ምልክት እግዚአብሔር ኢየሱስን አጽናኝ አድርጎ ለዓለም እንደሰጠ እኛም ለዓለም ሁሉ የምሥራቹን ቃል ማብሰር።”


**“.... ሕዝቤን አጽናኑ አጽናኑ” (ኢሳ. 40 :1)**

እኛ የአጽናኝቷ ማርያም ልውካን እህቶች እና አባቶች በብፁዕ ዮሴፍ አላማኖ አማካኝነት ቶሪኖ በሚባል በጣሊያን ከተማ ገዳማችን ተመሰረተ።

የተጠራነውም በፍቅር እንድንኖርና በተጠራንበት የፍቅር ሕይወት የእግዚአብሔርን ቃል ላልሰሙት ለማብሰር። ይህንንም የምናደርገው በሕብረት በመኖር፣ ዛሬ በምንገኝባቸው አገሮች፣ በአፍሪቃ፣ በእስያ፣ በአውሮፓ፣ በሰሜንና በደቡብ አሜሪካ ከማህበረሰቡ ጋር በመኖር የተለያየ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንገኛለን።

**የገዳማችንን መንፈስ ለመከተልም ሆነ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር እና መፅናናት ላልደረሳቸው ለማድረስ ለምትሹ እህቶች/ ወንድሞች ሁሉ -** የገዳማችን መጠይቅ እንደሚከተለው ነው

1. በቅድሚያ ራሷን/ራሱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት መስጠት የምትፈልግ/ የሚፈልግ
2. የእግዚአብሔርን ቃል ላልደረሳቸው ማብሰርና የተልኮ ሕይወት ለመኖር ሙሉ ፍላጎት ያላት/ ያለው
3. 10+3 ወይም ዲፕሎማ 12+3 Degree (ዲግሪ) ከዛም በላይ በማንኛውም ዘርፍ የትምህርት ማስረጃ ያላት/ ያለው
4. ለአባቶች 12ኛ ክፍል ይቀበላሉ



Our Lady of Consolata
Pray for Us

**“ታላቅነቴን በሕዝቦች መካከል ያውጃሉ” (ኢሳ. 66 :18)**

ስልክ
**0912-14-26-37**
**011-3-21-01-47 / 48**

የፖ.ሳ ቁጥር
**145069 / 22748**

አድራሻ
**ኮንሰላታ ሲስተሮች/ አባቶች አዲስ አበባ መካኒሳ ከመካነየሱስ ሴሚናሪ ፊት ለፊት**

## The Services Provided by EWWCSc

- Water Wells Drilling
- Water Works Construction
- Water Works Study and Design
- Construction of Irrigation Schemes
- Spring Development
- Rehabilitation and cleaning of old water wells
- Repair and Maintenance of water works construction machinery
- Import and Distribution of machinery, rigs, water pumps, Generators, Pipes and casings including its productions
- Different water scheme constructions (pipes lying, water reservoirs, stand for water reservoirs, water points, distribution lines, sanitation and hygiene facility etc...)
- Import and Distribution of General Electro Mechanical equipment & installation (supply and installation of water pumps & generators, renewable energy sources such as solar pumps, wind pumps and water power pumps)
- Contract Administration and Bill of Quantity preparation
- Purchase and Procurement of water works machinery, equipment and construction materials
- Different Training development on water works
- Engage in rental Activity of Construction machinery and equipment
- Import and as well as production of construction materials and distributions
- Engage in Share Exchange (purchase and sell of stock)
- Engage in Production of purified water, Seal and sales

## በአዲስ አበባ ካቶሊክ ሃገረስብከት ሴቶች ዕድገት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕከል

(ካሀሴዕማ/ቴ/ሙ/ት/ስ) አ.አ.

**Catholic Archdiocese Women's Promotion Technical and Vocational Education & Training Center**

(CAWPC / TVET) A. A

**“Come and see us. You will be most welcome! WE ARE WAITING FOR YOU!”**

በዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የሚገኙና የቀለም ትምህርታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች አቋርጠው የሙያ ሥልጠና ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶች ለማገዝ በአነስተኛ ክፍያ የሥልጠና አገልግሎት በማግኘት ለሥራ ብቁ የሚያደርጉና ለገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴ የሚያዘጋጁ የሙያ ሥልጠናዎችን በመስጠት ላይ እንገኛለን።

**በአጫጭር ሥልጠና**
**(Short training)**
በደረጃ አንድና በደረጃ ሁለት
Level (1) one and Level (2) two

**የሚሰጡ ሥልጠናዎች**

1. ልብስ ቅድና ስፌት
2. ህትመትና ማቅለም
3. የተሻሻለ የሽመና ሥራ
4. ጥልፍ በእጅና በስፌት መኪና
5. ሹራብ በእጅና በማሽን
6. ምግብ ዝግጅትና መስተንግዶ


ሀ - ከ 3-6 ወራት አጭር ኮርስና
ለ - ለ 10 ወራት በመረጡት ሙያ ሰልጥነው እራስዎን ለሥራ ያዘጋጁ።

**በማዕከአችን የሥልጠና አገልግሎቱ ቀጣይነት በጥራት የሚያመርታቸውን የዕደጥበብ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ በመግዛት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንጋብዛልን።**

**አድራሻችን**
አራዳ ክ/ከ ፒያሳ
ካቶሊክ ካቴደራል ት/ቤት
ቅጥር ግቢ ውስጥ

**ስልክ ቁጥር**
011 111 4786 / 011 157 5927

**E-mail**
cawpc@ethionet.et



**ስለ“ፍቅርና ሰላም ጋዜጣ” አስተያየት ካለዎት በስልክ ቁ. (0111) 55 03 00 በመደወል ለፍቅርና ሰላም ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ያካፍሉን!**



ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የሕፃናት እንክብካቤ እና ጥበቃ ቢሮ ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**“ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው አለሁና።” (ማቴ.18:20)**

LINK

No. 265 June 2024 P. O. Box 2454 Tel. (0111) 55 03 00 Addis Ababa

You are most welcome to
Subscribe and Advertise on LINK

## Message Of His Holiness Pope Francis For The

# First World Children's Day

25-26 May 2024



*Dear Children!*

Your first World Day, which will be held in Rome on 25-26 May this year, is fast approaching. That is why I thought of sending you a Message. I am happy that you will be able to read it and I thank all those responsible for passing it on to you.

I want to speak to each of you, dear children, because, as the Bible teaches us, and as Jesus showed so often, "you are precious" in God's eyes (Is 43:4).

At the same time, I am addressing this Message to all of you, because all children, everywhere, are a sign of every person's desire to grow and flourish. You remind us that we are all children, brothers and sisters. We would not be alive unless others brought us into this world, nor could we grow without having others to love and from whom to receive love (cf. Fratelli Tutti, 95).

All of you, girls and boys, are a source of joy for your parents and your families, but also for our human family and for the Church, in which each of us is like a link in a great chain stretching from the past to the future and covering the whole earth. That is why I encourage you to pay attention to the stories of grown-ups: your moms and dads, your grandparents and great grandparents. And not to forget all those other children and young people who are already battling illness and hardship, in hospital or at home, and those who even now are being cruelly robbed of their childhood. I think of children who are victims of war and violence, those experiencing hunger and thirst, those living on the streets, those forced to be soldiers or to flee as refugees, separated from their parents, those prevented from going to school, and those who fall prey to criminal gangs, drugs or other forms of slavery and abuse. Let us listen to their voices. We need to hear those voices, for amid their sufferings they remind us of reality, with their tearful eyes and with that tenacious yearning for goodness that endures in the hearts of those who have truly seen the horror of evil.

Dear young friends, in order for us and our world to grow and flourish, it is not enough to be united with one another; we need, above all else, to be united with Jesus. From him we receive a great deal of courage. He is always close to us, his Spirit goes before us and accompanies us on all the world's pathways. Jesus told us: "Behold, I make all things new" (Rev 21:5); this is the theme I have chosen for your first World Day. These words invite us to become as clever as children in grasping the new realities stirred up by the Spirit, both within us and around us. With Jesus, we can dream of the renewal of our human family and work for a more fraternal society that cares for our common home. This starts with little things, like saying hello to others, asking permission, begging pardon, and saying thank you. Our world will change if we all begin with these little things, without being ashamed to take small steps, one at a time. The fact that we are small reminds us that we are also frail and need one another as members of one body (cf. Rom 12:5; 1 Cor 12:26).

That is not all. The fact is that we cannot be happy all by ourselves, because our joy increases to the extent that we share it. Joy is born of gratitude for the gifts we have received and which we share in turn and it grows in our relationships with others. When we keep the blessings we have received to ourselves, or throw tantrums to get this or that gift, we forget that the greatest gift that we possess is ourselves, one another: all of us, together, are "God's gift." Other gifts are nice, but only if they help us to be together. If we don't use them for that purpose, we will always end up being unhappy; they will never be enough.

Instead, when we are all together, everything is different! Think of your friends, and how great it is to spend time with them: at home, at school, in the parish and the playground, everywhere. Playing, singing, discovering new things, having fun, everyone being together and excluding no one. Friendship is wonderful and it grows only in this way: through sharing and forgiving, with patience, courage, creativity and imagination, without fear and without prejudice.

Now, I am going to share a special secret with you. If we really want to be happy, we need to pray, to pray a lot, to pray every day, because prayer connects us directly to God. Prayer fills our hearts with light and warmth; it helps us to do everything with confidence and peace of mind. Jesus constantly prayed to the Father. Do you know what Jesus called him? In his language, he simply called him "Abba", which means "Daddy" (cf. Mk 14:36). Let's do the same thing! We will always feel that Jesus is close to us. He himself promised us that, when he said, "For where two or three are gathered in my name, there am I in the midst of them" (Mt 18:20).

WORLD CHILDREN'S DAY
ROME 2024

Dear children, you may know that in May, many of us will be together in Rome, to be together with children from all over the world. To prepare well for this, I would ask all of you to pray the same prayer that Jesus taught us – the Our Father. Recite it every morning and every evening, in your families too, together with your parents, brothers, sisters and grandparents. But not just by saying the words! Think about those words that Jesus taught us. He is calling us and he wants us to join actively with him, on this World Children's Day, to become builders of a new, more humane, just and peaceful world. Jesus, who offered himself on the Cross to gather all of us together in love, who conquered death and reconciled us with the Father, wants to continue his work in the Church through us. Think about this, especially those of you who are preparing to receive First Communion.

God has loved us from all eternity (cf. Jer 1:5). He looks upon us with the eyes of a loving father and a gentle mother. He never forgets us (cf. Is 49:15) and every day he accompanies us and renews us with his Spirit.

Together with the Most Blessed Virgin Mary and Saint Joseph, let us pray in these words:

Come, Holy Spirit,
show us your beauty,
reflected in the faces
of children all over the the world.
Come, Jesus,
you who make all things new,
who are the way that leads us to the Father,
come and remain with us always.
Amen.

*Rome, Saint John Lateran, 2 March 2024*
*FRANCIS*

This page is sponsored by CAFOD/SCIAF/TROCAIRE

**"But store up for yourselves treasures in heaven, where moths and vermin do not destroy, and where thieves do not break in and steal" (Matthew 6:20)**

# Our Lady, Terror of Demons




## *We are in a war, a spiritual war. The Christian life is a constant war against the world, the flesh, and the devil.*

But what does that mean? We are at war with "the world" in its fallen state, in which the world around us, fallen and prone-to-evil human society, attempts to lead us away from God and the Kingdom of Jesus Christ. We are at war with "the flesh," which does not mean our physical bodies per se, but our fallen human nature that is prone to temptation and sin. And we are at war with "the devil," by which we mean all the fallen angels, all of the spiritual realm that is in open rebellion against God our Creator and Redeemer.

When Lucifer rebelled against God, he rejected the idea that God was going to enter the universe in physical form, that Almighty God was going to become Incarnate. He who is all-powerful and eternal would take upon Himself the nature of a servant, that God would become a man. "I will not serve!" was Lucifer's cry, and he was cast out of heaven by St. Michael the Archangel, and became "Satan," our "Enemy." Even now, St. Michael is invoked by Christians in the fight against the power of Satan and his attempts to attack us as individual Christians, and to attack the Church as the Body of Christ.

But there is someone who Satan fears and hates even more than he fears St. Michael. His greatest enemy (of creatures) is the Blessed Virgin Mary, the Mother of God Incarnate. While we often think of Mary as the "Queen of the Angels," we can just as readily call her the "Terror of Demons." Can you imagine how the evil spirits must hate the fact that "the Woman," (Genesis 3:15; see also John 2:4 and 19:26) will crush the head of Satan? She who they observed as a young virgin in Nazareth, who gave birth to the Christ Child while herself still a teenager, is the one who will defeat them in union with her Divine Son! So, when you feel like you are under attack by the powers of hell, and when you feel alone and without aid, remember that you are NOT alone, and you can call on the Mother of God to come to your aid. You can invoke her as the "Queen of Angels," and ask her to send more angels to guard and defend you, and you can also invoke her as the "Terror of Demons," and ask her to crush the evil spirits who are afflicting you.

I would like to share with you an image and a litany which was put together by Fr. Augustine Wetta, OSB, of St. Louis (Benedictine) Abbey (St. Louis, Missouri). May we pray it fervently, and know that Mary will be there, along with her Divine Son and the holy angels, to defend and protect us in our spiritual warfare against the devil and his minions.

*September 3, 2022*
*by Fr. Ben Cameron Leave a Comment*
*confraternityofourladyofmercy.org*

### Warror's Litany to Our Lady

Queen of Angels, *pray for us.*
Queen of Heaven, *pray for us.*
Tower of David, *pray for us.*
Our Lady of Victories, *pray for us.*
Valiant Woman, *pray for us.*
Bulwark of the Faithful, *pray for us.*
Invincible Warrior, *pray for us.*
New Ark of the Covenant, *pray for us.*
Stronghold of God, *pray for us.*
Guardian of Christ, *pray for us.*
Mighty Mistress, *pray for us.*
Woman of might, *pray for us.*
Invincible Wall, *pray for us.*
Sworn Enemy of Satan, *pray for us.*
Deliverer of Christian Nations, *pray for us.*
Empress of the Golden Throne, *pray for us.*
Terror of the Demons of Hell, *pray for us.*

SAINT LOUIS ABBEY
https://www.stlouisabbey.org
fraugustine@priory.org

## የጸሎት ሐዋርያነት

ሰኔ
ከሀገራቸው በስደተኛነት
ለወጡ ሰዎች

ከጦርነት ወይም ከረሀብ በመሸሽ
በአደጋ እና በእንግልት መካከል
ለማለፍ ለሚገደዱ ስደተኞች
በሚሄዱባቸው
ሀገራት ጥሩ አቀባበል እና
የተመቻቸ የኑሮ እድል እንዲያገኙ
ስለስደተኞች እንጸልይ።

June
For Those Fleeing Their Own Countries

Let us pray that migrants fleeing from war or hunger, forced to undertake journeys fraught with danger and violence, may find welcome and new living opportunities in their host countries.



### የማቅረቢያ ጸሎት

ኢየሱስ ሆይ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ንፁህ ልብ አማካይነት የዚህን ቀን ጸሎቴን ፣ሥራዬን፣ ደስታዬን፣ ሐዘኔንና ሥቃዬን በመላው ዓለም ከሚቀደሰው ቅዳሴ ጋር አንድ አድርጌ ለአንተና ለቅዱስ ልብህ ሐሳቦች አቀርባለሁ፤ ለነፍሳት ደኅንነት፣ ለኃጢአት ካሣና ለክርስቲያኖች አንድነት፣ ለጳጳሳትና ለጸሎት ሐዋርያነት ማኅበር በተለይም ለዚህ ወር በርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ለተሰጡት ሐሳቦች አቀርባለሁ።

This page is sponsored by CRS

**"Can any one of you by worrying add a single hour to your life?" (Matthew 6:27)**

# LINK















ወንጌልን በጋራ እንስበክ

ሌሎች ቢያነቡዋቸው ትምህርት ያገኙባቸዋል ብለው የሚያምኑባቸውን መጣጥፎች እና የወንጌል አስተምህሮዎች ይላኩልን

ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ ስልክ - (0111) 55 03 00 ፋክስ (0111) 55 31 13 E-Mail - scpr@eccsdco.org